# ትንቢተ አሞጽ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

አሞጽ የቴቁሔ ሰው ነበረ (1፥1)፤ ቴቁሔም ከቤተ ልሔም በስተደቡብ 10 ኪሎ ሜትር ያህል፣ ከኢየሩሳሌም ደግሞ 17.8 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነበረች። አሞጽ እንደ ኢሳይያስ የአደባባይ ሰው ወይም እንደ ኤርምያስ ካህን አልነበረም። ይኖር የነበረው በግ በማርባትና የወርካ ፍሬ በመልቀም ነበር (1፥1፤7፥14-15)። በጎቹና ወርካው የእርሱ ይሁኑ ወይም ተቀጥሮ ይሥራ የሚታወቅ ነገር የለም። የቃል አጠቃቀም ችሎታው፣ ስለ ታሪክና ስለ ዓለም ያለው ሰፋ ያለ ዕውቀትና ግንዛቤ ሲታይ አሞጽ መሃይም ገበሬ ነበር ለማለት ያዳግታል። አሞጽ ነዋሪነቱ በይሁዳ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር በሰሜኑ መንግሥት ማለትም በእስራኤል ላይ የተናገረውን ፍርድ ለማስታወቅ ወደዚያ ተላከ። አብዛኛውን ጊዜ ያገለገለውም የእስራኤል ዋነኛ የአምልኮ ስፍራ በሆነችው፣ በቤቴል (7፥10-13፤ የዘፍ12፥8 ማብ ይመ) እንደ ሆነ ይገመታል። መጽሐፉ የተጻፈው ለሰሜኑ መንግሥት ብቻ ሳይሆን፣ ለደቡቡም መንግሥት ጭምር ነው ይሁዳና ኢየሩሳሌምም ተጠቅሰው የሚገኙት ለዚሁ ነው።

### የተጻፈበት ጊዜና ታሪካዊ ዳራው

በመጀመሪያ ቍጥር ላይ እንደ ተጠቀሰው፣ አሞጽ ትንቢት የተናገረው በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመነ መንግሥትና (792-740 ዓ.ቅ.ክ) በእስራኤል ንጉሥ በዳግማዊ ኢዮርብዓም (793-753 ዓ.ቅ.ክ) ዘመነ መንግሥት ነበር። የአገልግሎቱ ዋና ክፍል የተከናወነው 760-750 ዓ.ቅ.ክ ገደማ ሊሆን ይችላል። በዚህን ጊዜ ሁለቱም መንግሥታት እጅግ ከመበልጸጋቸውም በላይ፣ በፖለቲካና በወታደራዊ አቋማቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር (ከ2ነገ14፥23-15፥7፤ 2ዜና 26 ጋር ያነጻጽሩ)። ደግሞም ይህ ወቅት የጣዖት አምልኮ የነገሠበት፣ ስድ የቅንጦት አኗኗር የሰፋበት፣ ልቅ ግብረ ሥጋ የሚፈፀምበት፣ ፍትሕ የተጓደለበትና ድኻ የሚጨቈንበት ጊዜ ነበር። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የሰሜኑን መንግሥት በምርኮ አሳልፎ በአሦር እጅ ሰጠው (722-721 ዓ.ቅ.ክ)።

በዚህ ወቅት እስራኤላውያን ፖለቲካዊ ዋስትና ያገኙበትና በመንፈሳዊ ነገር የተኰራሩበት ጊዜ ነበር። ኤልያስ ከአርባ ዓመት በፊት፣ በአገልግሎቱ መጨረሻ አካባቢ፣ የእስራኤል ኀይል እንደ ገና እንደሚያንሠራራ ትንቢት ተናግሮ ነበር (2ነገ13፥17-19)፤ ከዚያም በኋላ በቅርቡ እስራኤል ታድሳ ከሰሎሞን ጊዜ ወዲህ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ ክብር እንደምታገኝ ዮናስ ተንብዮ ነበር (2ነገ14፥25)። ስለዚህ እስራኤል በእግዚአብሔር ታላቅ ጸጋ ውስጥ እንዳለች እርግጠኛ ሆና ነበር፤ ነገር ግን ብልጽግና ለመንፈሳዊ ሕይወቷ ንቅዘት ምክንያት እየሆነ መጣ። ታማኝ ባለመሆኗ እግዚአብሔር ቀደም ሲል ያመጣባት ቅጣት ተረሳ፤ ትዕግሥቱም ተዘነጋ። እግዚአብሔርም አሞጽ ይህንኑ ቅጣቱንና ትዕግሥቱን እንዲያሳስብ ላከው።

ከአሞጽ መጽሐፍ ጀምሮ የነቢዩ መጻሕፍት በቋሚነት ተሰባስበው እንዲቀመጡ ተደርጎአል። እነዚህም በመጻሕፍት መልክ በአንድነት ተሰብስበው፣ ሊመጣ እስካለው እስከ እስራኤል ውድቀትና ከዚያም ባሻገር በሄደችበት ሁሉ ከእርሷ ጋር ኖረዋል። (አሞጽ ከሆሴዕና ከዮናስ ጋር በአንድ ዘመን ስለ ኖረ፣ የእነዚያንም መግቢያ ይመልከቱ።)

### መሪ ሐሳቡና መልእክቱ

ዐበዮት የሆነው የትንቢቱ መሪ ሐሳብ በ5፥24 ላይ በግልጽ ተጠቅሶአል፤ ይኸውም በኅብረተ ሰብ ውስጥ ፍትህ መንገስ የእውነተኛ አምልኮ ዐይነተኛ ባሕርይ መሆኑ ነው። አሞጽ ስለ እግዚአብሔር የመመለስ ምልክት ኅብረተ ሰቡ ውስጥ ፍትሕ ሲሰፍን በመሆኑ ሕዝቡ ፍትሕን እንዲጠብቅ የቀረበ ጥሪ ነበር። ስለ እግዚአብሔር ፍርድና ጽድቅ አጥብቆ የሚናገር ሲሆን፣ ሆሴዕ ደግሞ ያተኰረው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ጸጋ፣ ምሕረትና ይቅርታ ላይ ነው። እግዚአብሔር ታማኝ ባልሆኑት፣ በማይ ታዘዙትና ቃል ኪዳን ባፈረሱት ሕዝቡ ላይ እንደሚፈርድ አሞጽ ተናግሮአል። እግዚአብሔር እስራኤልን በተለየ መንገድ ቢመርጣትም፣ ደግሞም ከግብፅ ሲያወጣትና በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን በውጊያ ሁሉ ድል በመስጠት ቸርነቱን ቢያበዛላትም፣ ሕዝቡ ዘወትር አላከበረውም፤ አልታዘዘውም። በቤቴል ያሉት ቤተ ጣዖቶችና ሌሎች የአምልኮ ስፍራዎች እንደ አረማውያን ሥርዐት ሆነዋል፤ እስራኤል፣ እግዚአብሔር ራሱ ለደነገገው የአምልኮ ሥርዐት እንኳ ዓለማዊ አመለካከት ነበራት። ሕዝቡ እግዚአብሔር የሚፈልገው ሥርዐተ አምልኮን መፈጸም ብቻ ነው ብለው ያስቡ ነበር፤ ይህንንም ከፈጸሙ በኋላ ሄደው እንደ ማንኛውም አረማዊ ደስ ያሰኛቸውን ያደርጉ ነበር፤ ያለ እግዚአብሔር ሕግም ስለሚኖሩ የክፉና የበጎ መለኪያ አልነበራቸውም። አሞጽ በሌሎች ትከሻ ራሳቸውን ለማግነን ወይም ለማበልጸግ የሚጥሩትን ሁሉ ያወግዛል። ሁለት ያማሩ ቤቶች (3፥15)፣ በውድ ዋጋ የተገዙ የቤት ዕቃዎችና እጅግ ያጌጡ ጠረጴዛዎች ያሏቸው ሁሉ ይህን ያገኙት ፍትሕ በማዛባትና ድኻውን በመጨቈን በመሆኑ፣ ሀብታቸው ሁሉ ጠፍቶ ባዶአቸውን ይቀራሉ።

በእስራኤል ላይ ሊሆን ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ እንዳለፈው ጊዜ (4፥6-11) ለማስጠንቀቅ ያህል ብቻ የሚደረግ መጠነኛ ቅጣት ሳይሆን፣ ፍጹም የሚያጠፋ ነው፤ ያልታሰበ ነገርም በደጅ ነው፤

ይኸውም ለጊትነቱ ራሳቸውን በታማኝነት ስለ ላልቀደሱ፣ እግዚአብሔርም ምርጥ ሕዝቡ በአሕዛብ መንግሥት እጅ ተመንግለው እንዲወድቁ ያደርጋል:: ይህም ሆኖ እንኳ፣ ሕዝቡ በንስሓ ወደ እርሱ ከቀረቡ "የሰራዊት አምላክ እግዚአብሄር ለትሩፉ" (5፥15፤5፥4-6:14 ይመ) የሚል ተስፋ ነበር:: በእርግጥ በቅርብ ከሚሆነው ፍርድ ባሻገር፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ወደ ፊት አስደናቂና የከበረ ነገር አዘጋጅ ቶአል:: የዳዊት ቤት እንደ ገና እስራኤልን ይገዛል፤ በብዙ አገሮችም ላይ አስተዳደሩን ያሰፋል፤ እስራ ኤላውያንም እንደ ገና በተስፋዪቱ ምድር በሰላም ይቀመጣሉ፤ የወይን ጠጅ በመጠጣትና የምድሪቱን ፍሬ በመብላት ይደሰታሉ (9፥11-15):: የታሪክ ባለቤት የሆነው የእስራኤል አምላክ ምርጥ ሕዝቡን አይተውም፤ የወሰነውን የድነት ዕቅድ አይቀይርም::

አሞጽ ስለ እርሱ የሚናገረው እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ብቻ አምላክ አይደለም፤ እርሱ የሁሉም ሕዝቦች ገዥ ነው፤ የፈጠራቸውና (9፥7) ላደረጉትም ጥፋት ተጠያቂ የሚያደርጋቸው (1፥3-2፥3) እነርሱን ነው ዐላማውንም ይፈጽም ዘንድ አንዱን በሌላው ላይ ያስነሣል (6፥14):: እርሱ ፍጥረተ ዓለማትን ሁሉ የሚገዛ ታላቅ ንጉሥ ነው (4፥13፤5፥8፤ 9፥5-6):: የእስራኤል አምላክ በሁሉም ላይ ሉዐላዊ በመሆኑ የሰዎችን ሁሉና የዓለምን ታሪክ እንዲሁም ዕጣ ፈንታ በእጁ የያዘ ነው:: እስራ ኤል፣ እግዚአብሔር በወደ ፊቱ ሁኔታ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም ላይ ጌታ መሆኑን፣ እስራኤል ልታውቅ ይገባታል:: ለእርሷ ብቻ የተጠበቀ ባይሆንም፣ እስራኤል ይገባኛል በማለት ከእግዚአብሔር የምትጠይቀው የተለየ ነገር ነበራት:: በሌላም በኩል እስራኤል ማስታወስ ያለባት እግዚአብሔር ለእርሷ የገባውን ቃል ኪዳን ብቻ ሳይሆን፣ እረሷም ለእግዚአብሔር የገባችውን ኪዳናዊ ግዴታ ጭምር ነው::

**አስተዋፅኦ**

1. ርእሳዊ መግለጫ (1፥1)
2. የአሞጽ መልእክት መግቢያ (1፥2)
3. በሕዝቦች ላይ የሚሆን ፍርድ (1፥3-2፥16)
   ሀ. በሶርያ ላይ የተነገረ ፍርድ (1፥3-5)
   ለ. በጋዛ ላይ የተነገረ ፍርድ (1፥6-8)
   ሐ. በፊንቄ (ጢሮስ) ላይ የተነገረ ፍርድ (1፥9-10)
   መ. በኤዶም ላይ የተነገረ ፍርድ (1፥11-12)
   ሠ. በአሞን ላይ የተነገረ ፍርድ (1፥13-15)
   ረ. በሞዓብ ላይ የተነገረ ፍርድ (2፥1-3)
   ሰ. በይሁዳ ላይ የተነገረ ፍርድ (2፥4-5)
   ሸ. በእስራኤል ላይ የተነገረ ፍርድ (2፥6-16)
      (1) ድኾችን ያለ ርኅራኄ መጨቆን (2፥6-7)
      (2) ሃይማኖትን ያለ ገደብ ማርከስ (2፥7-8)
      (3) እስራኤል ከሌላው ጋር ስትነጻጸር ያላት ስፍራ (2፥9-2)
      (4) የጭቈና ሥርዐት ይጠፋል (2፥13-16)
4. በእስራኤል ላይ የተነገረ ትንቢት (3፥1-5፥17)
   ሀ. በተመረጠው ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ፍርድ (ም 3)
      (1) የእግዚአብሔር ፍርድ መታወጁ (3፥1-2)
      (2) የፍርድ አዋጅ እርግጠኝነት (3፥3-8)
      (3) የቅጣቱ ተግባራዊነት (3፥9-15)
   ለ. ንስሓ በማይገባ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ፍርድ (ም 4)
      (1) በቅምጥሎች ላይ የሚደርሰው ፍርድ (4፥1-3)
      (2) ከትክክለኛው መንገድ የወጣ ሃይማኖታዊ ሕይወት (4፥4-5)
      (3) ያለፈው ቅጣት ወደ ንስሓ አለመምራቱ (4፥6-11)
      (4) ልቡን ላደነደነ ሕዝብ ተስፋ የለውም (4፥12-13)
   ሐ. ፍትሕ በሚያጓድሉ ሕዝቦች ላይ የሚደርሰው ፍርድ (5፥1-17)
      (1) የሞት ሙሾ (5፥1-3)
      (2) ሕይወትን እንዲፈልጉ የተሰጠ ምክር (5፥4-6)
      (3) ፍትሕ በመጓደሉ የቀረበ ክስ (5፥7-13)
      (4) ሕይወትን እንዲፈልጉ የተሰጠ ምክር (5፥14-15)
      (5) ብልጽግና ወደ ሐዘን እንደሚለወጥ መነገሩ (5፥14-15
5. በምርኮ ስለ መወሰድ በግልጽ መነገሩ (5፥18-6፥14)
   1. እስራኤል ሃይማኖቷን ከመስመር የወጣ በማድረግ የተነገረባት የወዮታ መልእክት(5፥18-27)
   2. በእስራኤል ዐጕል መኩራራት ላይ የተነገረ የወዮታ መልእክት (6፥1-7)
   3. በዕቡይና ፍትሕ በማያውቅ ሕዝብ ላይ የተወሰነ የፍርድ ቃል(6፥8-14)
6. ስለ እግዚአብሔር አጸፋዊ ቅጣት የሚናገሩ ራእዮች (7፥1-9፥10)

ሀ. በይቅርታ የታለፈ ፍርድ (7፥1-6)
(1) የአንበጣ መንጋ (7፥1-3)
(2) የሚባላ እሳት (7፥4-6)
ለ. የማይቀረው ፍርድ (7፥7-9፥10)
(1) ቱንቢው (7፥7-7)
(ሀ) አሞጽ ያየው ራእይ (7፥7-9)
(ለ) የአሜስያስ አሞጽን መቃወሙና በአሜስያስ ላይ የተነገረው ፍርድ (7፥10-17)
(2) የቃርሚያ ፍሬ የሞላበት ዕንቅብ (ም 8)
(ሀ) አሞጽ ያየው ራእይ (8፥1-3)
(ለ) የራእዩ ትርጓሜ (8፥4-14)
(3) በመሠዊያው አጠገብ የቆመው ጌታ (9፥1-10)
(ሀ) አሞጽ ያየው ራእይ (9፥1-10)
(ለ) የራእዩ ትርጓሜ (9፥5-10)
7. የእስራኤል መመለስና የወደ ፊት በረከቷ (9፥11-15)
ሀ. የዳዊት ቤት እንደ ገና መነሣት (9፥11-12)
ለ. እስራኤል እንደ ዔድን ለምለም ወደ ሆነች የመመለስ ተስፋ ማግኘቷ (9፥13-15)

1 በቴቁሔ ከነበሩት እረኞች መካከል አንዱ
የሆነው አሞጽ፣ ዖዝያን የይሁዳ ንጉሥ
በነበረ ጊዜ እንዲሁም የዮአስ[ሀ] ልጅ ኢዮር
ብዓም የእስራኤል ንጉሥ በነበረ ጊዜ፣ ይኸ
ውም የምድር መናወጥ ከመሆኑ ከሁ
ለት ዓመት በፊት ስለ እስራኤል ያየውና
የተናገረው ቃል ይህ ነው፤
2 እርሱም እንዲህ አለ፤

"*እግዚአብሔር* ከጽዮን ድምፁን ከፍ አድርጎ
ያሰማል፤
ከኢየሩሳሌምም ያንጐደጒዳል፤
የእረኞች ማሰማሪያዎች ደርቀዋል[ለ]፤
የቀርሜሎስም ዐናት ጠውልጎአል።"

## በእስራኤል ጐረቤቶች ላይ የተሰጠ ፍርድ

3 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ስለ ሦስቱ የደማስቆ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
የብረት ጥርስ ባለው ማሄጃ፣ ገለዓድን
አሂዳለችና፤
4 የወልደ አዴርን ምሽጎች እንዲበላ፣ በአዛሄል
ቤት ላይ እሳት እሰዳለሁ።
5 የደማስቆን በሮች እሰባብራለሁ፤
በቤት ዔደን በትር የያዘውን፣
በአዌን[ሐ] ሸለቆ ያለውንም[መ] ንጉሥ እደመስሳለሁ፤
የሶርያም ሕዝብ ተማርኮ ወደ ቂር ይሄዳል"
ይላል *እግዚአብሔር*።

6 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ስለ ሦስቱ የጋዛ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመ
ልስም፤
ሕዝቡን ሁሉ ማርካ በመውሰድ፣
ለኤዶም ሸጣለችና።
7 ምሽጎቿን እንዲበላ፣
በጋዛ ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ።
8 በአስቀሉና በትር የያዘውን፣
የአሽዶድንም ንጉሥ[ሠ] እደመስሳለሁ፤
በፍልስጥኤም ካሉት የመጨረሻው ሰው
እስኪሞት ድረስ፣
እጄን በአቃሮን ላይ እዘረጋለሁ፤"
ይላል ጌታ *እግዚአብሔር*።

1፥1 2ሳሙ14፥2፤ 2ነገ14፥21፡23፤5፤ 2ዜና26፥23፤ ሆሴ1፥1፤ዘካ14፥5
1፥2 መዝ29፥3፤ ኢሳ42፥13፤ ኤር12፥4፤አሞ9፥3፤ ኢዩ3፥16
1፥3 ቍ6፡9፡11፡13፡ ኢሳ7፥8፤8፥4፤17፥1-3 ፤አሞ2፥6
1፥4 1ነገ19፥17፤ 20፥1፤2ነገ6፥24፤ 2ነገ8፥7-15፤ ኤር17፥27፤ 49፥23-27፤ ሕዝ30፥8
1፥5 1ነገ16፥9፤ ኢሳ7፥16፤22፥6፤ 37፥12፤ኤር49፥27፤5 1፥30፤ዘካ9፥1
1፥6 ቍ3፤ ዘፍ10፥19፤ 14፥8፤1ሳሙ6፥17፤ አብ1፥11፤ሶፎ2፥4
1፥8 2ዜና26፥6፤ መዝ81፥14፤ ኢሳ34፥8፤14፥28፤ 14፥28-32፤ ሕዝ25፥16፤ ሶፎ2፥4-7

[ሀ]1 *ዕብራይስጡ ዮአስ ያለው ለኢዮአስ ተለዋጭ ስም ሳይሆን አይቀርም።*
[ለ]2 *ወይም የእረኞች ሐዘን የሚሉ አሉ ።*
[ሐ]5 *ወይም ነዋሪዎች*
[መ]5 *አዌን የቃሉ ትርጒም ክፉት እንደ ማለት ነው*
[ሠ]8 *ወይም ነዋሪዎች*

1፥1 *እረኞች፤* የዕብራይስጡ ትርጒም በግ አርቢ ይለዋል፤ በብሉይ ኪዳን ይህ ቃል የተጠቀሰው ስለ ሞዓብ ንጉሥ በተነገረ ጊዜ ብቻ ነው (2ነገ3፥4)፤ የተለየ የዕብራይስጥ ቃል ከተጠቀመው ከ7፥14 ጋር ይህ ያነጻጽሩ። በመሠረቱ አሞጽ ለዕለት ኑሮው የሚያስፈልገውን ገቢ የሚያገኝበት ዋና ተግባሩ የነቢያት አገልግሎት አልነበረም፤ በቤተ መቅደስ አገልግሎት ተሳታፊ አልነበረም። *አሞጽ፤* ምናልባት አሜስያስ ለሚለው ስም በአጭሩ የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል (2ዜና 17፥16)፤ ትርጒሙም፣ "እግዚአብሔር ይሸከማል" ወይም "እግዚአብሔር ይደግፋል" ማለት ነው። *ዖዝያን፤* በዚህ መጽሐፍ መግቢያ፣ "የተጻፈበት ጊዜና ታሪካዊ ሁኔታ" የሚለውን ይመ (የኢሳ6፥1 ማብ ይመ)፡ *ኢዮርብዓም፤* 2ነገ14፥23 ይመ። *የምድር መናወጥ፤* ትዝታው የማይጠፋ እጅግ አስከፊ ክስተት ነው፤ ምናልባትም በዘካ14፥5 ላይ የተጠቀሰው ሳይሆን አይቀርም። ይህም ሊሆን የቻለው፣ ንጉሡ ዖዝያን ለካህን ብቻ የተመደበውን አገልግሎት በማከናወን (2ዜና 26፥16) ኀጢአት በመሥራቱ ምክንያት መሆኑን የሲፍ ወልደ ኮርዮን በጻፈው ታሪክ ገልጾአል። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የምድር መናወጥ፣ የተነገረው የፍርድ ቃል መፈጸሙን የሚያጠናክር ነው። *ያየው፤* መለኮታዊ በሆነ መንገድ የተገለጠለት ለማለት ነው።

*1፥2-2፥16፤* በሕዝቦች ላይ የተነገረ ተከታታይ ንግር ነው። አሞጽ፣ የእስራኤል ጎረቤት መንግሥታት ስለ ሠሩት የጭካኔ ተግባር የሚገባቸውን የፍርድ ቃል ከተናገረ በኋላ፣ የራሱ በሆኑትና የእግዚአብሔርን ሕግ በናቁት ሁለት መንግሥታት ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይናገራል። የእስራኤል ኀጢአት ከሌሎች መንግሥታት ኀጢያት ጋር ጐን ለጐን አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ መዘርዘሩ፣ እስራኤል ከአረማውያን ጎረቤቶቿ እኩል በኀጢአት መዘፈቋን የሚያመለክት ነው።

*1፥2፤* ዋና ሐሳቡን የያዘ ቅስ ሲሆን፣ ክፉ ነገር እንደሚመጣ የሚያመለክተው የአሞጽ መልእክት ፍሬ ነገር ነው። *ከጽዮን፤* እግዚአብሔር በተመረጠ ሕዝቡ መካከል በኢየሩሳሌም ምድራዊ ዙፋኑን ዘርግቶአል። ከዚያም በራሱ ሕዝብና በሌሎቹ ሕዝቦች ላይ ፍርዱን ይሰጣል። *ድምፁን፤* እረኛው አሞጽ የአንበሳ ጩኸት ሰምቶ እስራኤልን ያስጠነቅቃል፤ ይህም አንበሳ፣ ብቻውን የእስራኤል እረኛ ለመሆን የሚፈልገውን ራሱን እግዚአብሔርን ያመለክታል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነውን ሥዕላዊ አገላለጽ ኢዩ 3፥16 ይመ። *ማሰማሪያዎች ... የቀርሜሎስም ዐናት፤* 9፥3 ይመ። ከደረቁ እስከ ለምለሙ የምድሪቱ ክፍል ፈጽሞ እንደሚያጠፋ ከባድ ድርቅ የእግዚአብሔርም ፍርድ እንደዚያው ይሆናል።

1፥3 *ስለ ሦስቱ*...ኀጢአት...አራቱ፤ ስለ ብዙ ኀጢአታቸው በተለይም ስለ ተጠቀሰው (ቍ6፡9፡11፡13፤2፥1፡4፡6 ይመ) ለማለት ነው። ተመሳሳይ ስለ ሆነው አኃዛዊ አገላለጽ ምሳ6፥16፤ 30፥15፡18፡21፡29፤ሚክ 5፥5። *የደማስቆ፤* የአራማውያን ወይም የሶርያ ዋና ከተማ ናት፤ የምትገኘውም ከእስራኤል በስተ ሰሜን ሲሆን፣ በዚያ ዘመን የእስራኤል ጠላት ነበረች፤ ወንጀሏም በሸንፈቻቸው በገለዓድ ሰዎች ላይ የፈጸመችው ጭካኔ ነው፤ ገለዓድ የእስራኤል ግዛት ስትሆን፣ ከገሊላ በስተ ምሥራቅ የምትገኝ ነበረች። *ማሄጃ...አሂዳለችና፤* የእህል ፍሬ እንዲወጣ ከዕንጨት በተሠራ የመውቂያ መሣሪያ እህሉ በዐውድማ ላይ ይደበደባል ወይም የመውቂያ መንኰራኵር እንዲሄድበት ይደረጋል (ከኢዮ41፥30፤ ኢሳ28፥27፤ 41፥15 ጋር ያነጻጽሩ፤ 2ነገ13፥7 እና የሩት 1፥22ማብ ይመ)።

1፥4 *የወልደ አዴርን፤* ወይም ቤንሐዳድ ይባላል፤ እርሱም የአዛሄል ልጅ ሲሆን (2ነገ13፥24)፣ በዚህ ስም የተጠራ ሁለተኛው ንጉሥ ነው፤ የገዛውም ከ796-775 ዓ.ቅ.ክ. ነበረ (ከ2ነገ 8፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ)። *ምሽጎች፤* ቍ7፡10፡12፡ 14፤2፥2፡5 ይመ። ይህም የነገሥታትና የሀብታሞች መኖሪያ የሆኑ ምሽግ መሰል ቤተ መንግስቶችን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። *እንዲበላ... እሳትን እሰዳለሁ፤* ቍ7፡ 10፡12፤2፥2፡5 ይመ፤ ከቍ14 ጋር ያነጻጽሩ። ብዙውን ጊዜ መለኮታዊ ፍርድን ለማመልከት የሚጠቀስ አገላለጽ ነው። ፍርዱም ታላላቅ ከተሞችንና ምሽጎችን በሚያቃጥል አስከፊ ጦርነት ይገለጣል፤ በኤር17፥27፤ 49፥27፤50፥32፤ ሆሴ8፥14 የተጠቀሱትን ፍርዶች ይመ። *በአዛሄል፤* ከ842-796 ዓ. ቅ. ክ. የነበረ የደማስቆ ንጉሥ ሲሆን፣ የአዳዲስ ነገሥታትን ሥርወ መንግሥት የመሠረተ ነው (2ነገ8፥7-15 ይመ)።

1፥5 *በቤት ዔደን፤* በደማስቆ የሚገኘውን የአትክልት ስፍራ ሊያመለክት ይችላል። *በአዌን ሸለቆ፤* ከሊባኖስና በሊባኖስ ትይዩ ባሉት ተራሮች መካከል ያለው የቢቃ ሸለቆ ሳይሆን አይቀርም፤ ነገር ግን ደማስቆ ያለችበት የወንዝ ሸለቆ ብዙውን ጊዜ፣ "የክፋት ሸለቆ" ተብሎ የሚጠራው ሊሆን ይችላል (አማራጭ ትርጒሙን ይመ)። *ንጉሥ፤* በቁሙ በዙፋን ላይ የተቀመጠ ማለት ነው፤ ቍ8 ይመ። *ቂር፤* ያልታወቀ ቦታ ነው፤ ምናልባትም በዓላም አቅራቢያ የሚገኝና (2ነገ16፥9፤ ኢሳ22፥6) የደማስቆ አራማውያን የመጡበት ስፍራ (9፥7) ሳይሆን አይቀርም።

1፥6 *የጋዛ፤* ከአምስቱ የፍልስጥኤም ከተሞች አንዷ ስትሆን፣ ከግብፅ ወደ ፍልስጥኤም ምድር መሸጋገሪያ ላይ ትገኛለች። *ሕዝቡን ሁሉ፤* ቍ9 ይመ፤ በጦርነት የተማረኩትን ተዋጊዎች ብቻ ማለት አይደለም። ከኤዶም ወደ ጋዛ በሚያመራው የንግድ መሥመር ላይ ከይሁዳ በስተ ደቡብ ያሉትን መንደሮች የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። *ለኤዶም፤* ቍ9 ይመ፤ ሰዎችን እንደ ከብት ለሌሎች አገሮች ይሸጡ ነበር።

1፥8 *በአስቀሉና...የአሽዶድን...በአቃሮን፤* ሌሎች ሦስት የፍልስጥኤም ከተሞች ናቸው (የቍ6 ማብ ይመ)፤ ጌት የተባለው (ከ6፥2 ጋር ያነጻጽሩ) አምስተኛው የፍልስጥኤም ከተማ፣ በዖዝያን ሳይያዝ አልቀረም (2ዜና26፥6ይመ)። *የመጨረሻው፤* ምንም የሚቀር ሰው እንደሌለ ያመለክታል፤ ፍልስጥኤም በመጨረሻ በናቡከደነፆር ተደምስሳለች።

9 *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤*
“ስለ ሦስቱ የጢሮስ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን
አልመልስም፡፡
የወንድማማችነትን ቃል ኪዳን በማፍረስ፣
ሕዝቡን ሁሉ ማርካ ለኤዶም ሸጣለችና፡፡
10 ምሽጎችዋን እንዲበላ፣
በጢሮስ ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ፡፡”

11 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የኤዶም ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱም፣ ቍጣዬን አል
መልስም፤
ርኅራኄን[ረ] በመንፈግ፣
ወንድሙን በሰይፍ አሳዶታልና፤
የቍጣውንም ነበልባል ሳይገድብ፣
መዓቱን ሳያቋርጥ አውርዶበታልና፤
12 የባሶራን ምሽጎች እንዲበላ፣
በቴማን ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ፡፡”

13 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የአሞን ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
ድንበሩን ለማስፋት፣
የገለዓድን ነፍሰ ጡር ሴቶች ሆድ ቀዶአልና፡፡
14 በጦርነት ቀን በጩኸት ውስጥ፣
በማዕበል ቀን በዐውሎ ነፋስ ውስጥ፣
ምሽጎቿን እንዲበላ፣
በረባት ቅጥሮች ላይ እሳት እሰዳለሁ፡፡
15 ንጉሥዋ[ሰ] ከሹማምንቱ ጋር፣
በአንድነት ተማርኮ ይሄዳል፣”
ይላል እግዚአብሔር፡፡

# 2

1 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“ስለ ሦስቱ የሞዓብ ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
የኤዶምን ንጉሥ ዐጥንት፣
ዐመድ እስኪሆን ድረስ አቃጥሎአልና፤
2 የቂርዮትን ምሽጎች[ሸ] እንዲበላ፣
በሞዓብ ላይ እሳት እሰዳለሁ፤
ሞዓብ በጦርነት ጩኸትና በመለከት ድምፅ
መሓል፣
በታላቅ ሁካታ ውስጥ ይሞታል፡፡
3 ገዢን እደመስሳለሁ፣
አለቆቿንም ሁሉ ከንጉሥዋ ጋር እገድላለሁ፣”
ይላል እግዚአብሔር፡፡

4 *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤*
“ስለ ሦስቱ የይሁዳ ኀጢአት፣
ይልቁን ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
የእግዚአብሔርን ሕግ ንቀዋል፤
ትእዛዙንም አልጠበቁምና፤
አባቶቻቸው በተከተሏቸው[ቀ] አማልክት፣
በሐሰት[በ] አማልክት በመመራት ስተዋልና፡፡
5 የኢየሩሳሌምን ምሽጎች እንዲበላ፣
በይሁዳ ላይ እሳት እሰዳለሁ፡፡

## *በእስራኤል ላይ የተሰጠ ፍርድ*

6 *እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤*
“ስለ ሦስቱ የእስራኤል ኀጢአት፣
ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቍጣዬን አልመልስም፤
ጻድቁን ስለ ጥሬ ብር፣
ችግረኛውንም ስለ ጥንድ ጫማ
ይሸጡታልና፡፡

1፥9 ቍ3፤1ነገ5፥1፡12፤9፥11-14፤ኢር25፥22፤ኢል3፥4፤ማቴ11፥21
1፥10 ኢሳ23፥1-18፤34፥8፤ኤር47፥4፤ሕዝ26፥2-4፤ዘካ9፥1-4
1፥11 ዘኍ20፥14-21፤1ዜና28፥17፤መዝ63፥10፤83፥6፤ሕዝ25፥12-14፤ዘካ1፥15
1፥12 ዘፍ36፥11፡15፤ኢሳ34፥5፤63፥1-6፤ኤር25፥21፤ሕዝ25፥12-14፤35፥1-15፤አብ1፥1፤ሚል1፥2-5
1፥13 ዘፍ19፥38፤34፥29፤2ነገ8፥12፤ሕዝ21፥28፤ሆሴ13፥16
1፥14 ዘዳ3፥11፤ኢዮ39፥25፤ኢሳ30፥30፤ኤር23፥19
1፥15 1ዜና20፥1፤ኤር25፥21 ኤር49፥1፤ሕዝ21፥28-32፤
2፥1 ኢሳ16፥6፤33፥12
2፥2 ኢሱ6፥20፤ኢዮ39፥25፤ኤር48፥24
2፥3 መዝ2፥10፤ኢሳ15፥1-9፤16፥1-14፤40፥23፤ኤር48፥1፤ሕዝ25፥8-11፤ሶፎ2፥8-9
2፥4 ዘፀ34፥15፤ዘዳ31፥20፤2ነገ17፥19፤22፥13፤መዝ4፥2፤ኢሳ9፥16፤ኤር6፥19፤9፥14፤16፥12፤ሕዝ20፥24፤ሆሴ12፥2
2፥5 2ነገ25፥9፤2ዜና36፥19፤አሞ3፥11 ኤር 17፥27፤ ሆሴ 8፥14፤2፥6 ኢል3፥3፤አሞ1፥3፤8፥6

[ረ]11 ወይም *ሰይፍ ከእርሱ ጋር የተባበሩትን አጠፋ*
[ሰ]15 ወይም *ሞሎክ በዕብራይስጡ መልካም ነው*
[ሸ]2 ወይም *ከተሞቿ* የሚሉ አሉ ፡፡
[ቀ]4 ወይም *በውሸት* የሚሉ አሉ
[በ]4 ወይም *ውሸት* የሚሉ አሉ ፡፡

1፥9 *ጢሮስ፤ ታላቋ የፊንቄ የንግድ ከተማ ናት፡፡* በዳዊት ዘመን (1ነገ5፥1)በኋላም በሰሎሞን ጊዜ (2ነገ5፥12) ከእስራኤል ጋር የወዳጅነት ውል አድርጋ ነበር፤ ይህ የወዳጅነት ውል፣ ዐማቱ ጢሮስንና ሲዶናን በገዛው (1ነገ16፥30-31) በአክዓብ ዘመነ *መንግሥትም* ቀጥሎ ነበር፡፡ *ሸጣለችና፤* ወንጀሏ ፍልስጥኤም ከፈጸመችው ጋር ተመሳሳይ ነበር (ቍ6)፡፡

1፥10 *ቅጥሮች፤* ጢሮስ የማይደፈርና አስተማማኝ ጥበቃ ስላላት በራሷ የምትመካ ደሴት ነበረች (ከሕዝ26፥1-28፥19 ጋር *ያነጻጽሩ*)፡፡

1፥11 *የኤዶም፤* ከዔሳው ዘር የተገኘ ሕዝብ ነው (ዘፍ36*ይመ*፤ከዘፍ25፥23-30፤27፥39-40 ጋር *ያነጻጽሩ*)፡ *ወንድሙን፤* እስራኤልን ማለቱ ነው(ከአብ8-10 ጋር *ያነጻጽሩ*)፡፡ *ምናልባት “የወንድማማችነት ውል” የተባለውን ያመለክታል*(የቍ9 ማብ *ይመ*)፡፡ እንግዲህ የኤዶም ወንጀል ይህን ቃል ኪዳን አፍርሳ በጠላትነት *መቀጠሏ* ነበር፡፡

1፥12 *የባሶራ…በቴማን፤* የታወቁ የኤዶም ከተሞች ናቸው፡፡ ሁለተኛው በስተ ሰሜን 59 ኪሜ ያህል ከምትርቀው ከባዝራ ከተማ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ *የመጀመሪያው* ደግሞ በፔትራ አጠገብ እንደ ነበር ይገመታል፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ከተሞች ከጠፉ ኤዶም በተጠናከረ መልኩ ጦርነቱን የመቀጠል ብቃት አይኖራትም ማለት ነው፡፡

1፥13 *የአሞን፤* ፍርዱ ዛሬ አማን ተብላ በምትጠራው በረባት ከተማ ላይ ያተኵረ ነው (ዘዳ3፥11 ማብ *ይመ*)፡፡ እግዚአብሔር፣ *መሬትን ለመያዝ* ተስገብግበው ሰውን በጭካኔ የሚያጠፉትን *ለመቅጣት* በኀይለኞች ሰዎችና በተፈጥሮ ተጠቅሞ እንዲህ ዐይነቱ ጭካኔ እንዳይቀጥል አገሪቱን ያለመሪዎች ያስቀራል፡፡

*1፥14፤* ይህ በአሦራውያን ተፈጽሞአል፡፡

*1፥15፤* ኤር49፥3 እና የኤር 49፥1 አማራጭ ትርጉም *ይመ*፡፡

2፥1 *የኤዶምን ንጉሥ ዐጥንት… አቃጥሎአልና፤* የንጉሡ አስከሬን በክብር ሲቀበር መንፈሱ ዕረፍት እንደሚያገኝ ይታመን የነበረውን፣ በማቃለል በተጽዕኖ ሥር ለማዋል የተደረገ ነው፡፡

2፥2 *የቂርዮትን፤* “ከተሞች” የሚል ትርጒም ያለው በብዙ ቍጥር የተገለጸ ስም (አማራጭ ትርጒሙን *ይመ*) ወይም የትልቅ ከተማ ስም (ኤር48፥24 *ይመ*) እና የሞዓብ ሕዝብ አምላክ ቤተ ጣዖት ስም (1ነገ11፥7፡33 *ይመ*) ሊሆን ይችላል፡፡

2፥4 *የእግዚአብሔርን ሕግ ንቀዋል፤* ይሁዳ የሠራው የኀጢአት ዐይነት ከሌሎች *መንግሥታት* ኀጢአት የተለየ ነበር፡፡ እነዚያ *መንግሥታት* በአጠቃላይ የታወቁትን የሰውን ልጅ ሕጎች ሲጥሉ፣ ይሁዳ ግን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ አልታዘዘችም፡፡ እነዚህ ኀጢአቶች በእስራኤል ላይ በቀረበው የክስ ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ናቸው፡፡

2፥5 *ምሽጎች እንዲበላ… እሳትን፤* በይሁዳ ላይ የተወሰነው ቅጣት በአራም ወይም በሶሪያ(1፥4)፣ በጋዛ(1፥7)፣በጢሮስ(1፥10)፤ በኤዶም(1፥12)፣በአሞንና(1፥14)በሞዓብ ላይ (2፥2) ከተወሰነው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይህም የተመኩበትን ሀብትና መከላከያ የሚያወድም ነበረ፡፡

*2፥6፤* የእስራኤል ኀጢአት ሕዝቡ በአጠቃላይ ዘቅጦ የነበረበትን ሥነ ምግባራዊ ጒድለት አጋልጦአል፡፡ *ጻድቁን፤* ዕዳ የሌለባቸውንና በሕጉ መሠረት *መሸጥ* የማይገባቸውን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (ከዘሌ25፥39-43 ጋር *ያነጻጽሩ*)፡፡ *ችግረኛውንም፤* መረዳት እንደሚገባቸው እግዚአብሔር አዞአል (ዘዳ15፥7-11)፤ ነገር ግን ሊከፍሉ ቃል ገብተው አንድ ጥንድ ጫማ እንኳ ወስደው መክፈል ካቃታቸው፣ በዕዳው ምክንያት ባሪያ ሆነው ይሸጡ እንደ ነበረ ያመለክታል (8፥6 *ይመ*)

7 የድኾችን ራስ፣ በምድር ትቢያ ላይ
ይረግጣሉ፤
ፍትሕንም ከጭቍኖች ይነጥቃሉ፤
አባትና ልጅ ከአንዲት ሴት ጋር ይተኛሉ፤
እንዲህም እያደረጉ ቅዱስ ስሜን ያረክሳሉ።
8 በመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ፣
በየመሠዊያው ሥር ይተኛሉ፤
በአምላካቸው ቤት፣
በመቀጫነት የተወሰደውን የወይን ጠጅ
ይጠጣሉ።

9 ቁመቱ እንደ ዝግባ፣
ጥንካሬውም እንደ ባሉጥ ዛፍ የነበረ ቢሆንም፣
አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁት፣
ከላይ ፍሬውን፣
ከታችም ሥሩን አጠፋሁ።
10 "የአሞራውያንን ምድር ልሰጣችሁ፣
ከግብፅ አወጣኋችሁ፤
አርባ ዓመትም በምድረ በዳ መራኋችሁ።
11 ደግሞም ነቢያትን ከወንዶች ልጆቻችሁ
መካከል፣
ናዝራውያንንም ከጕልማሶቻችሁ መካከል
አስነሣሁ፤
የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ ይህ እውነት
አይደለምን?"
ይላል እግዚአብሔር።

12 "እናንተ ግን ናዝራውያኑን የወይን ጠጅ
አጠጣችኋቸው፤
ነቢያቱንም ትንቢት እንዳይናገሩ አዘዛችኋቸው።

13 "እነሆ፤ በእህል የተሞላ ጋሪ እንደሚያደቅ፣
እኔም አደቃችኋለሁ።
14 ፈጣኑ አያመልጥም፤
ብርቱውንም ብርታቱ አይረዳውም፤
ኀያሉም ነፍሱን አያድንም።
15 ቀስተኛው በቦታው ጸንቶ አይቆምም፤
ፈጣኑም ተዋጊ ሮጦ አያመልጥም፤
ፈረሰኛውም ነፍሱን አያድንም።
16 ጐበዞቹ ተዋጊዎች እንኳ፣
በዚያ ቀን ዕራቁታቸውን ይሸሻሉ፤"
ይላል እግዚአብሔር።

## በእስራኤል ላይ የተጠሩ ምስክሮች

3 የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እግዚአብሔር
በእናንተ ከግብፅ ባወጣሁት ሕዝብ ሁሉ
ላይ የተናገረውን ይህን ቃል ስሙ፤
2 "ከምድር ወገን ሁሉ፣
እናንተን ብቻ መረጥሁ፤
ስለዚህ ስለ ሠራችሁት ኀጢአት ሁሉ፣
እኔ እቀጣችኋለሁ።"

3 በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ፣
አብረው መጓዝ ይችላሉን?
4 አንበሳ የሚበላውን ሳያገኝ፣
በጫካ ውስጥ ይጮኻልን?
ምንም ነገርስ ሳይዝ፣
በዋሻው ውስጥ ያገሣልን?
5 ወጥመድ ሳይዘረጋ፣
ወፍ በምድር ላይ ይጠመዳልን?
የሚይዘው ነገር ሳይኖርስ፣
ወጥመዱ ከምድር ይፈነጠራልን?
6 የመለከት ድምፅ በከተማ ውስጥ ሲሰማ፣
ሰዎች አይደነግጡምን?
ጥፋትስ በከተማ ላይ ቢደርስ፣

2፥7 ዘሌ18፥21፤ አሞ5፥11-12፤8፥4
2፥8 ዘፀ22፥26፤ ዘዳ24፥12-13፤ ሆሴ7፥14፤አሞ4፥1፤ 6፥6፤ዕን2፥6
2፥9 ዘኍ13፥32፤ 21፥23-26፤ኢሱ10፥12፤2ነገ19፥30፤ ኢዮ18፥16፤ መዝ29፥9፤ ኢሳ10፥33፤ ሕዝ17፥9
2፥10 ዘፀ3፥8፤6፥6፤ 20፥2፤ዘኍ21፥25፤ ዘዳ2፥7፤8፥2፤ኢሱ 13፥4፤ አሞ3፥1፤9፥7
2፥11 ዘዳ18፥18፤ መሳ13፥5፤ኤር7፥25
2፥12 ኢሳ30፥10፤ ኤር11፥21፤አሞ7፥12-13፤ሚክ2፥6
2፥13 አሞ7፥16-17
2፥14 1ነገ20፥11፤ ኢዮ11፥20፤ መዝ33፥16፤ ኢሳ30፥16-17
2፥15 ዘፀ15፥21፤ መክ9፥11፤ሕዝ39፥3፤ ዘካ10፥5
2፥16 ኤር48፥41
3፥1 አሞ2፥10፤ ሰፎ2፥5
3፥2 ቀኍ14፤ ዘፀ19፥6፤ ዘዳ7፥6፤ኤር14፥10፤ ሚክ2፥3፤ሉቃ12፥47፤1ጴጥ4፥17
3፥4 መዝ104፥21፤ ኢሳ42፥13፤ሆሴ5፥14
3፥5 መዝ119፥110
3፥6 ዘኍ10፥2፤ ኢዮ39፥24፤ ኢሳ14፥24-27፤31፥2፤ ኤር4፥21

2፥7 *ይረግጣሉ፤* 8፥4 ይመ። *የድኾችን... ከጭቍኖች፤* ፍትሕ እንዳይጓደልባቸው እነዚህን መንከባከብና ለእነዚህም ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የእስራኤል ሕግ በግልጽ ያዛል (ዘፀ 23፥6-8)፤ እንዲሁም በቅርብ ምሥራቅ አገሮች ሁሉ የነበሩ ነገሥታት እንዲህ ዐይነት ሰዎች መንከባከብ ይጠበቅባቸው ነበር። *አባትና ልጅ ከአንዲት ሴት ጋር ይተኛሉ፤* አባትና ልጅ በጋራ የሚያመነዝሩባት ይህች ሴት በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለች የቤት ሠራተኛ ትሁን አትሁን የታወቀ ነገር የለም። ያም ሆነ ይህ ከአንዲት ልጃ ገረድ ጋር ግብረ ሥጋ ከተፈጸመ በሕጉ መሠረት ጋብቻ መፈጸም ግዴታ ይሆናል (ዘፀ22፥16፤ዘዳ 22፥28-29)። አባትና ልጅ በጋራ ከአንዲት ልጃ ገረድ ወይም አንዲት ሴት ጋር ዝሙት መፈጸም በሕጉ በጥብቅ የተከለከለ ነበር (ዘሌ18፥7-8፥15፤ 20፥11-12)። *ቅዱስ ስሜንም ያረክሳሉ፤* ከዘሌ 18፥21፤19፥12፤ 20፥3፤21፥6፤22፥2፥32፤ኤር 34፥16፤ ሕዝ20፥9፤ጋር ያነጻጽሩ።

2፥8 *በመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ፤* በሕጉ መሠረት የአንድ ሰው የሌሊት ልብስ በመያዣነት ወስዶ ማሳደር ክልክል ነው (ዘፀ22፥26-27፤ ዘዳ24፥12-13)፤ እንዲሁም የመበለትን ልብስ መውሰድ የተከለከለ መሆኑ ተጠቅሶአል (ዘዳ24፥17)። *በየመሠዊያው ሥር... በአምላካቸው ቤት፤* ድኾችን የሚንከባከበውን ሕግ የሚጥሱ፣ እስራኤላውያን ያለአግባብ ያካበቱ ትን ሀብት ቅዱስ ተብለው በሚታመኑ ስፍራዎች እንኳ ሳይቀር ይጠቀሙባቸው ነበር። *በመቀጫነት፤* ለተሠራው ጥፋት ወይም ለደረሰው ጉድለት ካሣ የሚሆንን ነገር ነው። ከመጠን በላይ የሆነ ክፍያ መጠየቅ ወይም ጉዳት ደርሶአል ብሎ የሐሰት ክስ መመሥረት የተለመደ ነበር።

2፥9 *አጠፋሁት፤* እስራኤል የእግዚአብሔርን ሕግ በማወቋ ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ታምራዊ ርዳታ በማግኘትም የታደለች ነበረች። *አሞራዊውን፤* በከነዓን የሚኖሩትን ሁሉ ያመለክታል (የዘፍ10፥16፤15፥16፤ መሳ6፥10 ማብ እንዲሁም ዘዳ7፥1 እና ማብ ይመ)። *ከላይ ፍሬውን፣ ከታችም ሥሩን፤* ሁሉንም በአጠቃላይ ማለት ነው።

2፥10 *አወጣኋችሁ፤* 3፥1 ይመ። እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት ለእስራኤላውያን የሰጠው ታላቅ በረከት ሲታይ፣ የእስራኤል በደል ያንኑ ያህል የጎላ ነው፤ በዚህም ስፍራ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ካቀረባቸው ክሶች አንዱ ክፍል ሆነው ተጠቅሰዋል።

2፥11 *ነቢያትን... ናዝራውያንንም ...አስነሣሁ፤* የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት የሚናገሩ ነቢያትና (ዘዳ18፥15-19) ለእርሱ የተለዩት ናዝራውያን (ዘኍ6፥1-21፤ መሳ13፥5) ለሕዝቡ ልዩ ስጦታ ይሆኑ ዘንድ የተመረጡ ናቸው። ከካህናት ወገን ያልሆኑት እነዚህ ሰዎች፣ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ይሆንለት ዘንድ ሕዝቡን ወደ እርሱ ለመጥራት በቃልም ሆነ በተግባር በምሳሌነት የሚጠቀምባቸው ናቸው።

2፥12 *እናንተ ግን* የእግዚአብሔርን ታማኝ አገልጋዮች በከፍተኛ ደረጃ በማሳሳት፣ እግዚአብሔር በመካከላቸው በሚሠራው ሥራ ላይ ዕምፀዋል (ከ7፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

*2፥13፤* የተጫነ ጋሪ ከሥሩ የሚወድቀውን ሁሉ ያደቃል።

*2፥14-16፤* ጸንቶ መቆም ይችላል ተብሎ የሚገመተው ወይም ማምለጥ ይችላል ተብሎ የሚታሰበው ማንም ቢሆን ራሱን ማዳን አይችልም።

2፥16 *በዚያ ቀን፤* የሰሜኑ መንግሥት በአሦር በተደመሰሰ ጊዜ እንደ ሆነው ሁሉ፣ እግዚአብሔር በፍርድ የሚመጣበትን ቀን ያመለክታል።

*3፥1-5፥17፤* በእስራኤል ላይ የተወሰነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ እርግጠኛነት የሚያመለክት ንግግር የያዘ ክፍል ነው።

3፥1 *ይህን ቃል ስሙ፤* 4፥1፤5፥1 ይመ። ለሠሩት ኀጢአት ምላሽ ይሰጡ ዘንድ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠራቸዋል። በ1፥2-2፥16 ላይ ከተገለጠው በላይ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር በቀጥታ ይናገራል።

3፥2 *እናንተን ብቻ፤* በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ካገኙት ብርታትና ብልጥግና የተነሣ በመልካም ደረጃ ላይ በመሆናቸው የእግዚአብሔር ምርጥ ስለሆንን ነው ወደሚል አጉል መዝናናት መርተአቸዋል። ከተደረገላት መልካም ነገር ባሻገር ልትወጣው የሚገባትን ኀላፊነት ለብዙ ጊዜ ስለ ዘነጋች በሚያስደነግጥ ሁኔታ እንድታስተውል ትደረጋለች።

*3፥3-6፤* አሞጽ እንዲህ ዐይነት አስደንጋጭ ቃላት ለምን

ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?
7በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን
ለአገልጋዮቹ ለነቢያት ሳይገልጥ፣
ምንም ነገር አያደርግም።

8አንበሳ አገሣ፤
የማይፈራ ማን ነው?
ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ፤
ትንቢት የማይናገር ማን ነው?

9ለአዛጦን ምሽግ፣
ለግብፅም ምሽግ እንዲህ ብላችሁ ዐውጁ፤
"በሰማርያ ተራሮች ላይ ተሰብሰቡ፤ በውስጧ
ያለውን ታላቅ ሁከት፣
በሕዝቧም መካከል ያለውን ግፍ እዩ።"
10 "ቅሚያንና ዝርፊያን በምሽጋቸው ውስጥ
የሚያከማቹ፣
በጎ ነገር ማድረግን አያውቁም፤ "
ይላል እግዚአብሔር።

11ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"ጠላት ምድሪቱን ይወራል፤
ምሽጎቻችሁን ያፈርሳል፤ ድንኳኖቻችሁን
ይዘርፋል።"
12እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"እረኛ ከአንበሳ መንጋጋ፣
ሁለት የእግር ዐጥንት ወይም የጆሮ ቍራጭ
እንደሚያድን፣
እንዲሁም በሰማርያ
በዐልጋቸው+ ጫፍ ላይ፣
በደማስቆም በምንጣፋቸው ላይ የተቀመጡ፣
እስራኤላውያን ይድናሉ።"
13"ይህን ስሙ፤ በያዕቆብም ቤት ላይ መስክሩ"
ይላል ጌታ፣ ሁሉን የሚገዛ አምላክ እግዚአብሔር ።
14"እስራኤልን ስለ ኀጢአቷ በምቀጣበት ቀን፣
የቤቴልን መሠዊያዎች አፈርሳለሁ፤
የመሠዊያው ቀንዶች ይቈረጣሉ፤
ወደ ምድርም ይወድቃሉ።
15የክረምቱን ቤት፣
ከበጋው ቤት ጋር እመታለሁ፤
በዝሆን ጥርስ ያጌጡ ቤቶችም ይደመሰሳሉ፤
ታላላቅ አዳራሾችም ይፈርሳሉ፤"
ይላል እግዚአብሔር።

## እስራኤል ወደ እግዚአብሔር አልተመለሰም

4 እናንተ በሰማርያ ተራራ የምትኖሩ የባሳን
ላሞች፣
ድኾችን የምትጨቍኑና ችግረኞችን
የምታስጨንቁ፣
ባሎቻችሁንም፣ "መጠጥ አቅርቡልን"
የምትሉ ሴቶች ይህን ቃል ስሙ፣
2ጌታ እግዚአብሔር በቅድስናው እንዲህ
ሲል ምሎአል፤
"እነሆ፤ በመንጠቆ ተይዛችሁ የምትወሰዱበት፣
ትሩፋናችሁ እንኳ በዓሣ መንጠቆ
የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል።
3እያንዳንዳችሁ በቅጥሩ በተነደለው መሽሎኪያ

3፥7 ዘፍ18፥17፤ 1ሳሙ3፥7፤ኤር23፥2 2፤ዳን9፥22፤ዮሐ15፥15፤ራእ10፥7
3፥8 አሳ31፥4፤ 42፥13፤ኤር20፥9፤ ዮና1፥1-3፤3፥1-3፤ ሐሥ4፥20
3፥9 ኢሱ13፥3፤ 2ዜና26፥6፤አሞ4፥1፤ 6፥1
3፥10 መዝ36፥3፤ አሞ5፥7፤6፥12፤ ሚክ6፥10፤ ዕን2፥8፤ሶፎ1፥9
3፥11 አሞ2፥5፤ 6፥14
3፥12 ሳሙ17፥34፤ አስ1፥6፤አሞ6፥4
3፥13 ሕዝ2፥7
3፥14 ቍ2፤ ዘፍ12፥8፤ዘፀ27፥2፤ ዘሌ26፥18፤ አሞ5፥5-6
3፥15 መሳ3፥20፤ 1ነገ22፥39፤ ኢሳ34፥5፤ ኤር36፥22፤ ሆሴ10፥5-8፡ 14 –15፤ አሞ5፥11፤6፥11
4፥1 ዘዳ24፥14፤ መዝ22፥12፤ ኢሳ58፥6፤ ኤር44፥19፤ ሕዝ18፥12፤ አሞ2፥8፤3፥9፤ 5፥11፤8፥6
4፥2 2ነገ19፥28፤ 2ዜና33፥11፤ ኢሳ19፥8፤ኤር31፥31፤አሞ6፥8 4፥3 ሕዝ12፥5

+12 በዕብራይስጡ ለዚህ ዐረፍተ ነገር የተሰጠው ትርጒም አይታወቅም

እንደ ተጠቀመ ለመግለጽ የንጽጽር ሐሳቦችን በያዙት በእነዚህ መልስ አዘል ጥያቄዎች አማካኝነት ከቍ7-8 ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ጽፎአል። እያንዳንዱ ሥዕላዊ መግለጫ ከዕለታዊ የአኗኗር ዘይቤ ጋር የተዛመደ ሲሆን በመለኮታዊ ድርጊት የሚጠቃለል (ቍ6) ምክንያትና ውጤት አለው።

3፥8 *አንበሳ፤* በ1፥2 ላይ የተገለጸውን ሐሳብ ያስተጋባል። *ትንቢት የማይናገር ማን ነው?* አሞጽ የሚናገረው፣ እግዚአብሔር ስለ ተናገረ ነበረ።

*3፥9፤* በሰማርያ ምሽጎች ውስጥ ያለ አግባብ ሀብት ባካበቱት ላይ እግዚአብሔር ላቀረበው ክስ ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ የፍልስጥኤምና የግብፅ ኀያላንና ባለ ጠጎች ተጠርተዋል(ቍ15 ይመ)። *ምሽግ፤* የ1፥4 ማብ ይመ። *ታላቅ ሁከት* ፤ በግል ጥቅም ላይ ያተኰረ የሥልጣን መዋቅር፣ ደንታ ቢስነትና በዐመፀኝነት የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ የሚያመጣው ውጤት ነው። በዓመፅ እንዲሁም በግል ጥቅም ላይ ያተኰረው የሥልጣን መዋቅር ውጤት ነው።

3፥10 *የሚያከማቹ፤* ከ2፥6-8 ጋር ያነጻጽሩ። የእስራኤል ብልጽግና በጭቈናና በዝርፊያ ላይ የተመሠረተ ነበር፤ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶችም የሚያመለክቱት በእንዲህ ዐይነቱ ስግብግብነት ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣውን ፍርድ ነው (ከዕን2፥6-11 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥11 *ጠላት፤* አሦርን ለማለት ነው። *ምሽጎቻችሁን፤* ሰማርያ በስግብግብነትና በዝርፊያ ባከማቸችው ሀብት የተሞላውን ምሽግ ያመለክታል።

3፥12 *እረኛ...ሁለት የእግር ዐጥንት ...እንደሚያድን፤* በጉ በእረኛው አለመሰረቁንና በዱር አውሬ መበላቱን ለባለቤቱ የሚያረጋግጥ ነው። *ይድናሉ፤* ጒዳት የደረሰባቸው ቅሬታዎች ብቻ ይተርፋሉ ማለት ነው። ሕዝቡ መቍሰል ብቻ ሳይሆን ጥፋትም ይደርስበታል። *የተቀመጡ፤* በምቾት ሥራ ፈተው የተቀመጡትን ለማለት ነው (ከ6፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። *በደማስቆም በምንጣፋቸው ላይ፤* አማራጭ ትርጒሙን ይመ፤ በዚህ ጊዜ እስራኤል ግዛቷን እስከ ደማስቆ አስፋፍታ ስለ ነበር፣ የሰማርያ ሀብታም ነጋዴዎች በዚያች ከተማ ካላቸው የንግድ ጥቅም በተጨማሪም ምቹና ያጌጡ ቤቶችን ሳይሠሩ አልቀሩም (ከ1ነገ 20፥34 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥13 *ስሙ...መስክሩ፤* በቍ9 ላይ ለተጠቀሱት የሚናገር ነው። የፍልስጥኤምና የግብፅ ኀያላንና ባለ ጠጎች የተጠሩት እግዚአብሔር በሰማርያ ኀያላንና ባለ ጠጎች ላይ ያቀረበውን ክስ እንዲሰሙና ትክክል መሆኑን እንዲሁም ፍርዱ የሚገባ መሆኑን እንዲመሰክሩ ነው። እነዚህ አረማውያን እንኳ ሳይቀሩ በእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛነት ይስማማሉ።

3፥14 *የቤቴልን መሠዊያዎች፤* የእስራኤል ኀጢአት ቀዳማዊ ኢዮርብዓም በቤቴል በተከለው ቤተ ጣዖት ውስጥ ሥር ሰዶ ነበር (1ነገ12፥26-33)። *የመሠዊያው ቀንዶች፤* ለተወገዙት ሰዎች የተሠራ የመጨረሻው መሸሸጊያ እንኳ (ከ1ነገ1፥50-53 ጋር ያነጻጽሩ) እስራኤልን ከፍርድ ሊያድናት አይችልም።

3፥15 *የክረምቱን ቤት ከበጋው ቤት፤* ከ6፥11 ጋር ያነጻጽሩ። በፍርድ ቀን ብልጥግና ባለቤቱን ሊደግፍ እንደማይችል የሚያሳይ ተጨማሪ ምልክት ነው፤ ወይም ከውጭ የመጡ እጅግ ውድ ጌጣጌጦች፣ ቅርጻ ቅርጾችና ከዝሆን ጥርስ የተሠሩ ጌጦችም ቢሆኑ ከፍርድ ቀን ሊያድኑ አይችሉም (ከ6፥4፤ 1ነገ22፥39 ጋር ያነጻጽሩ)። የእነዚህ ቅርጻ ቅርጽ ቅሬታዎች በሰማርያና በሌሎች ከተሞች በሚገኙ የቤተ መንግሥት ፍርስራሾች ውስጥ ተገኝተዋል።

4፥1 *ይህን ቃል ስሙ፤* የ3፥1 ማብ ይመ። *የባሳን ላሞች፤* መልእክቱ በቀጥታ የሚመለከተው ከመሳፍንት ወገን የሆኑትን ሴቶች ሲሆን፣ ተነጻጽረው የቀረቡትም በጥንቷ ከነዓን በዮርዳኖስ ማዶ ሰሜናዊ ክፍል በሚገኘው ለምለም መስክ ከሚሰማሩትና ከሚደልቡት ምርጥ ከብቶች ጋር ነው (ከመዝ22፥12፤ሕዝ39፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። በተለዋጭ የገባው ዘይቤ ለስድብ ይሁን ወይም ለማሞካሸት የታወቀ ነገር የለም።

4፥2 *ጌታ እግዚአብሔር... ምሎአል፤* የሁኔታውን አሳሳቢነትና የድርጊቱ መፈጸም እርግጠኛነት ያመለክታል። *በቅድስናው፤* ከእስራኤል ኀጢአት ጋር ተነጻጽሮ የቀረበ ነው። እግዚአብሔር በራሱ በኩል እንዳደረገው ሁሉ፣ እነርሱም በበኩላቸው ቃል ኪዳኑን በታማኝነት ቢጠብቁ ኖሮ ምን ሊሆኑ ይችሉ እንደ ነበር ያመለክታል (ዘፀ19፥6)። *በመንጠቆ፤* የአሦራውያን የድንጋይ ላይ ሥዕሎች እንደሚያመለክቱት የጦር እስረኞች አፍንጫቸውን ወይም የታችኛው ከንፈራቸውን ተበስተው መንጠቆ ይደረግባቸውና በገመድ ይጐተቱ ነበር (ከ2ነገ19፥28፤ 2ዜና33፥11፤ ሕዝ19፥4፡9፤ ዕን1፥15 ጋር ያነጻጽሩ)። የዕብራይስጡ ትርጒም ገመድን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

4፥3 *በቅጥሩ በተነደለው መሽሎኪያ፤* 2ነገ17፥5 ይመ። *ሬማንም፤*

ወደ ሬማንም[*] ትጣላላችሁ፤”
ይላል እግዚአብሔር።

4 “ወደ ቤቴል ሂዱና ኀጢአትን ሥሩ፤
ወደ ጌልገላም ሂዱና ኀጢአትን አብዙ፤
በየማለዳው መሥዋዕቶቻችሁን፣
በየሦስቱ[¹] ዓመት ዐሥራታችሁን አቅርቡ።
5 እርሾ ያለበትን እንጀራ የምሥጋና
መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ፤
በፈቃዳችሁም በምታቀርቡት ቊርባን
ተመኩ፤
እናንት እስራኤላውያን በእነርሱም ተኵራሩ፤
ማድረግ የምትወዱት ይህን ነውና፤”
ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

6 በየከተማው ሆዳችሁን ባዶ አደረግሁት፤
በየመንደሩም የምትበሉትን አሳጣኋችሁ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም”
ይላል እግዚአብሔር።

7 “መከር ሊደርስ ሦስት ወር ሲቀረውም፣
ዝናብ ከለከልኋችሁ፤
በአንዱ ከተማ ላይ አዘነብሁ፤
በሌላው ላይ ግን እንዳይዘንብ አደረግሁ፤
አንዱ ዕርሻ ሲዘንብለት፣
ሌላው ዝናብ አጥቶ ደረቀ።
8 ሰዎች ውሃ ፍለጋ ከከተማ ወደ ከተማ ባዘኑ፣
ይሁን እንጂ ጠጥተው አልረኩም፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፤”
ይላል እግዚአብሔር።

9 “የአትክልትና የወይን ቦታዎቻችሁን ብዙ
ጊዜ መታሁ፤
በዋግና በአረማሞም አጠፋኋቸው፤
አንበጦችም የበለስና የወይራ ዛፎቻችሁን በሉ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፤”
ይላል እግዚአብሔር።

10 “በግብፅ ላይ እንዳደረግሁት፣

4፥4 ዘኍ28፥3፤ ዘዳ14፥28፤ኢሱ7፥2፤ ሕዝ20፥39፤ ሆሴ4፥15፤አሞ5፥21-22፤4፥5ዘሌ7፥13፤ 22፥18 –21
4፥6 ኢሳ3፥1፤ 9፥13፤ኤር5፥3፤ ሐጌ2፥17
4፥7 ዘፀ9፥4:26፤ ዘዳ11፥17፤2ዜና7፥13 ፤ኢሳ5፥6፤ኤር3፥3፤ ዘካ14፥17
4፥8 ኢዩ36፥31፤ ኤር3፥7፤14፥4፤ ሕዝ4፥16-17 ሐጌ1፥6
4፥9 ዘፀ10፥13፤ ዘዳ28፥22፤ኢሳ9፥13፤ ኤር3፥10፤ ኢዩ1፥7፤2፥25
4፥10 ዘፀ9፥3፤ 11፥5፤ ዘዳ28፥21፤ኢሳ9፥13: 17፤34፥3
4፥11 ዘፍ19፥24፤ ኢዮ36፥13፤ ኢሳ7፥4፤ ኤር23፥14፤ይሁ1፥23
4፥13 መዝ65፥6፤13 5፥7፤ኢሳ47፥4፤ ዳን2፥28፤አሞ5፥8:27 ፤9፥6፤ሚክ1፥3
5፥1 ኤር4፥8፤ ሕዝ19፥1
5፥2 2ነገ19፥21፤ ኤር14፥17፤50፥32፤ አሞ8፥14

መቅሠፍትን ላክሁባችሁ፤
ከተማረኩት ፈረሶቻችሁ ጋር፣
ጕልማሶቻችሁን በሰይፍ ገደልሁ፤
የሰፈራችሁ ግማት አፍንጫችሁ እንዲገባ
አደረግሁ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም”
ይላል እግዚአብሔር።
11 “ሰዶምንና ገሞራን እንደ ገለበጥኋቸው፣
አንዳንዶቻችሁን ገለበጥሁ፤
ከእሳት እንደ ተነጠቀ ትንታግ ሆናችሁ፤
እናንተ ግን ወደ እኔ[ᵀ] አልተመለሳችሁም፤”
ይላል እግዚአብሔር።

12 “ስለዚህ እስራኤል ሆይ፤ እንደዚህ
አደርግብሃለሁ፤
እንደዚህም ስለማደርግብህ፣ እስራኤል
ሆይ፤
አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ።”

13 ተራሮችን የሚሠራ፣
ነፋስን የሚፈጥር፣
ሐሳቡንም ለሰው የሚገልጥ፣
ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ፣
የምድርንም ከፍታዎች የሚረግጥ፣
ስሙ የሰራዊት አምላክ
እግዚአብሔር ነው።

## የእስራኤል ሕዝብ ለንስሓ መጠራት

5 የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለ እናንተ የምደ
ረድረውን ይህን የሙሾ ቃል ስሙ፤
2 “ድንግሊቱ እስራኤል ወደቀች፤
ከእንግዲህም አትነሣም፤

[*]3 በተለምዶ የዕብራይስጥ ቃላት የተከፈለው የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቅጅ (የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ይመ) የሞቁና ተራራ ሆይ ራቅ ይላል።
[¹]4 በየሦስቱ ቀናት ዐሥራታችሁን የሚሉ አሉ
[⁶]6 ዕብራይስጡ ጥርሳችሁን አጠራለሁ ይላል።
[ᵀ]11 ዕብራይስጡ አምላክ ይላል።

የቦታ ስም እንደ ሆነ ይገመታል (አማራጭ ትርጉም ይመ)

*4፥4-5፤* በምፀት የተነገረ ቃል ነው።

4፥4 *ቤቴል ... ጌልገላ፤* እነዚህ ከተሞች እግዚአብሔር ባደረገው ርዳታ የመታሰቢያ በዓል የሚከበርባቸው ቦታዎች ስለ ሆኑ በታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ተሰጥቶአቸዋል (ከዘፍ35፥1-15፤ኢሱ4፥20–24 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሁለቱም ቦታዎች በአሞጽ ዘመን የታወቁ የአምልኮ ስፍራዎች ነበሩ (5፥5፤ከሆሴ4፥15፤9፥15፤12፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። *በየማለዳው መሥዋዕቶቻችሁን፤* ዘፀ29፥38-42 ይመ። *ዓመት፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። “ቀኖች” የሚለው ቃል በዕብራይስጡ ትርጉም አንዳንድ ጊዜ፣ “ዓመቶች” የሚለውን ይተካል። *ዐሥራታችሁን፤* በየሦስት ዓመቱ የሚቀርብ ልዩ ዐሥራት ሳይሆን አይቀርም (ከዘዳ14፥28፤26፥12ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥5 *እርሾ ያለበትን እንጀራ ፤* እርሾ ያለበትን እንጀራ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ አጥብቆ የተከለከለ ነበር (ዘሌ6፥17፤7፥12 ይመ)። እስራኤላዊያንን በድፍረት የእግዚአብሔ ርን ሕግ በመተላለፋቸው አሞጽ ይገሥጻቸዋል፤ ወይም አጠቃላይ በሆነ መንገድ ተገቢ ያልሆነ ስጦታን ለጌታ ማቅረብን ይናገራል። እርሾ ያለበት ዳቦ ከኅብረት መሥዋዕት ጋር ሊቀርብ ይችላል (ዘሌ7፥13ይመ)። *ማድረግ የምትወዱት፤* የሃይማኖትን ሥርዐትና ወግ ይወዳሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የሚወደውን ማለትም በጎነትን፣ ምሕረትን፣ ቸርነትንና ፍትሕን አይወዱም ነበር (5፥15፤ ኢሳ5፥7፤ 61፥8፤ ሆሴ6፥6፤ ሚክ6፥8 ይመ)።

*4፥6-11፤* ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማስጠንቀቅና ለመቅጣት የተፈጥሮን አደጋ እንዲደርስባቸው ያደርግ ነበር፤ ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ መማር ሲገባቸው ፈጥነው ይረሱ ነበር (ከዘዳ28፥22:39-40:42:48:56-57 ጋር ያነጻጽሩ)።

*4፥6፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሥቃይ የተፈጥሮ አደጋ የሚያስከትለውን ጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚመጣ መቅሠፍት ነው (3፥6)። *ግን... እኔ* ቍ8-11 ይመ።

*4፥7-8፤* ከመከር በፊት ሦስት ወር ሙሉ ዝናብ ካልዘነበ የእህሉ እድገት የተገታ ይሆናል።

4፥9 *አንበጦች፤* ከ7፥1፤ኢዩ1፥4 ጋር ያነጻጽሩ።

4፥10 *በግብፅ እንዳደረግሁት መቅሠፍት፤* ዘፀ7፥14- 12፥30 ይመ።

4፥11 *ሰዶምንና ገሞራን፤* የፍጹም ጥፋት ምሳሌ ናቸው። በእነዚህ ከተሞች ላይ እግዚአብሔር ያመጣው ፍርድ (ዘፍ19፥24-25 ይመ) ምሳሌያዊ አነጋገር ሆኖአል (ከዘዳ29፥23፤ ኢሳ1፥9፤ 13፥19፤ ኤር49፥18፤50፥40፤ ሰፎ2፥9ጋር ያነጻጽሩ)። *ከእሳት እንደ ተነጠቀ ትንታግ፤* በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ የዳኑ ለማለት ነው (ከዘካ3፥2 ጋር ያነጻጽሩ)።

4፥12 *አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ፤* በአሦራውያን ታላቅ ጥፋት ደርሶባት የተንበረከከችው እስራኤል፣ በሲና ተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ከገባችና እርሱን ካስቈጣችው እግዚአብሔር ጋር ትገናኛለች።

*4፥13፤* የ5፥8-9 ማብ ይመ። እንዲህ ዐይነት ግርማና ኀይል ያለው ታላቅ አምላክ በቍ12 ላይ የተገለጠውን ፍርድ በቀላሉ መፈጸም ይችላል።

5፥1 *ይህን ... ቃል ስሙ፤* የ3፥1 ማብ ይመ። *ይህን የሙሾ፤* እስራኤል እንደ ሞተች በመቊጠር አሞጽ የሐዘን እንጒርጒሮውን ያሰማል።

5፥2 *ድንግሊቱ እስራኤል፤* ኤር18፥13፤31፥4:21ይመ። እንዲሁም የ2ነገ19፥21፤ ኢሳ23፥12 ማብ ይመ። *ተጣለች፤* በሚዳ ላይ

በገዛ ምድሯ ተጣለች፤
የሚያነሣትም የለም።"

3ጌታ *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"አንድ ሺህ ብርቱዎችን ለእስራኤል
የምታዘምት ከተማ፣
አንድ መቶ ብቻ ይቀሯታል፤
አንድ መቶ ብርቱዎችን የምታዘምተውም፣
ዐሥር ብቻ ይቀሯታል።"
4*እግዚአብሔር* ለእስራኤል ቤት እንዲህ
ይላል፤
"እኔን ፈልጉ፤ በሕይወትም ትኖራ
ላችሁ።"
5ቤቴልን አትፈልጉ፤
ወደ ጌልገላ አትሂዱ፤
ወደ ቤርሳቤህም አትሻገሩ፤
ጌልገላ በእርግጥ ትማረካለች፤
ቤቴልም እንዳልነበረች[ሀ] ትሆናለችና።
6*እግዚአብሔርን* ፈልጉ፤
በሕይወትም ትኖራላችሁ፤
አለበለዚያ እንደ እሳት የዮሴፍን
ቤት ያወድማል፤
እሳቱም ቤቴልን ይበላል፤ የሚያጠፋውም የለም።
7እናንት ፍትሕን ወደ መራርነት
የምትለውጡ፣
ጽድቅንም ወደ ምድር የምትጥሉ ወዮላችሁ!
8ሰባቱን ከዋክብትና ኦሪዮንን የሠራ፣
ጨለማውን ወደ ንጋት ብርሃን የሚለውጥ፣
ቀኑን አጨልሞ ሌሊት የሚያደርግ፣
የባሕሩንም ውሃ ጠርቶ፣
በገጸ ምድር ላይ የሚያፈስ፣
ስሙ እግዚአብሔር ነው፤
9እርሱ በብርቱው ላይ ድንገተኛ ጥፋትን፣
በተመሸገውም ከተማ ላይ ውድመትን
ያመጣል።
10እናንተ በፍርድ አደባባይ
የሚገሥጻችሁን ትጠላላችሁ፤
እውነት የሚናገረውንም ትንቃላችሁ።
11እናንተ ድኻውን ትረግጣላችሁ፤
እህል እንዲሰጣችሁም
ታስገድዱታላችሁ፤
ስለዚህ በተጠረበ ድንጋይ ቤት ብትሠሩም፣
በውስጡ ግን አትኖሩም፤
ባማሩ የወይን ተክል ቦታዎች ወይን
ብትተክሉም፣
የወይን ጠጁን ግን አትጠጡም፤
12ኀጢአታችሁ ምንኛ ታላቅ እንደ ሆነ፣
በደላችሁም የቱን ያህል እንደ በዛ እኔ
ዐውቃለሁና።
ጻድቁን ትጨቊናላችሁ፤
ጉቦም ትቀበላላችሁ፤
በፍርድ አደባባይም ከድኻው ፍትሕ
ትነጥቃላችሁ።
13ስለዚህ አስተዋይ ሰው በእንዲህ ያለ ጊዜ
ዝም ይላል፤
ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና።
14በሕይወት ትኖሩ ዘንድ፣
መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ፤
ከዚያ በኋላ እንደ ተናገራችሁት፣
የሰራዊት ስምሳክ *እግዚአብሔር*
ከእናንተ ጋር ይሆናል።
15ክፉውን ጥሉ፤ መልካሙንም ውደዱ፤
በፍርድ አደባባይም ፍትሕን አታንድሉ፤

5፥3 ኢሳ6፥13፤ አሞ6፥9
5፥4 ዘዳ4፥29፤ 32፥46-47፤ ኢሳ55፥3፤ ኤር29፥13፤ ሕዝ18፥9
5፥5 ዘፍ21፥31፤ 1ሳሙ7፥16፤8፥2፤ 11፥14፤ሆሴ4፥15፤ አሞ8፥14
5፥6 ቍ14፤ ዘሌ18፥5፤ኢዩ4፥24፤ መዝ22፥26፤105፥4፤ ኢሳ31፥1፤55፥6፤ ኤር4፥4፤አሞ3፥14፤ ክሶፎ2፥3
5፥7 ኢሳ5፥20፤ ሆሴ10፥4፤ አሞ3፥10፤6፥12
5፥8 ዘፍ1፥16፤ ኢዮ38፥12፡31፤ መዝ104፥20፤ 104፥6-9፤ኢሳ42፥16፤ ኤር16፥21፤አሞ4፥13 18፥9
5፥9 ሚክ5፥11
5፥10 1ነገ22፥8፤ ኢሳ29፥21፤ገላ4፥16
5፥11 ዘዳ28፥30፤ መሳ9፥27፤አሞ3፥15፤ 4፥1፤8፥6፤9፥14፤ ሚክ1፥6፤6፥15፤ ሶፎ1፥13
5፥12 ኢዩ5፥4፤ 36፥18፤ ኢሳ1፥23፤ 5፥23፤ኤር5፥28፤ ሕዝ22፥12፤ ሆሴ5፥3፤አሞ2፥6-7
5፥13 አስ4፥14፤ ሚክ2፥3
5፥14 ቍ6
5፥15 ዘፍ18፥25፤ መዝ52፥3፤97፥40፤ኢሳ1፥17፤29፥1፤ ኤር36፥3፤ኢል2፥14፤መክ5፥7-8፤7፥18፤ ዘካ8፥16፤ሮሜ12፥9

[ሀ]5 ሐዘን

---

እንደ ተጣለ በድን ተተወች ማለት ነው (ከኤር9፥22 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥3 *ከተማ፤* የዕብራይስጡ ትርጒም፣ ሁሉም ችግር የሚገጥማቸውን የተለያየ ብዛት ያላቸውን የኅብረተ ሰብ ክፍሎች ያመለክታል።

5፥4 *ፈልጉ፤* ቍ6፡14 ይመ። *በሕይወትም፤* እግዚአብሔርን ሲፈልጉ በአሞጽ እንጕርጕሮ ውስጥ ከተተነበየው አሠቃቂ ሞት ያመልጣሉ (ቍ15)

5፥5 *ቤቴልን ... ጌልጌላ፤* የ4፥4 ማብ ይመ። *ቤርሳቤህም፤* ከይሁዳ በስተ ደቡብ የሚገኝ ሲሆን፣ የጣዖት አምልኮ የሚካሄድብትና ሰዎች በየጊዜው ለአምልኮ የሚጓዙበት ስፍራ ነበር (ከ8፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ብቻ እንዳይመለክ ያደረገ በጣዖት አምልኮ የረከሰ ስፍራ ሁሉ ይጠፋል።

*5፥6፤* የጣዖት አምልኮ የሚካሄድባቸው ስፍራዎች በሙሉ ጠፍተዋል፤ ይሁን እንጂ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰች እንደ ገና እንደ አንድ መንግሥት የመደራጀት ተስፋ አላት። ይህ ካልሆነ ግን ሕዝቡ እንዲሁ ይጠፋል። *የዮሴፍን ቤት፤* የሰሜኑ መንግሥት (እስራኤል) የዮሴፍ ልጅ በሆነው በኤፍሬም ነገድ ይመራ ነበር (ቍ15፤ 6፥6 ይመ)። *ቤቴልን፤* የሰሜኑ መንግሥት ዋነኛ የሃይማኖት ማዕከል ናት (7፥13፤3፥14፤ 4፥4፤ 7፥10 ይመ)። እስራኤላውያን በዚያ የሚያመልኩት የጣዖት አምላክ እውነተኛው አምላክ ሊፈርድ ሲመጣ ስፍራውን ከጥፋት ለማዳን ኀይል አይኖረውም።

5፥7 *ፍትሕን ወደ መራርነት የምትለውጡ፤* የፍትሕ ተቋሞች የሚሰጡትን ሕጋዊ ሥርዐት በማዛባት ፍርድ ቤቶች ኢፍትሐዊ ተግባር የሚፈጸምባቸው የምሬት ቤቶች አደረጓቸው። ሕጉን ቸል በሚልና እውነተኛውን ሃይማኖት በሚንቅ ኅብረተ ሰብ መካከል የእግዚአብሔርን ሥርዐት ማመሰቃቀል የማይቀየር ነው (6፥12ይመ)።

*5፥8-9፤* በ 4፥13 ላይ እንዳለው በዚህ ቦታ አጠር ያለ መዝሙር ገብቶአል (9፥5-6 ይመ)፤ አሞጽ በዚህ ስፍራ በጎውን ወደ ክፉ "የምትለውጡ" (ቍ7) በሚለውና ሌሊትን ወደ ቀን፣ "የሚለውጥ" እንዲሁም ሕዝቡ ከበስተ ጀርባው የተደበቁበትን ቅጥር ማፍረስና የፍጥረተ ዓለምን ሥርዐት መቈጣጠር የሚችል ኀይል ባለው እግዚአብሔር መካከል ያለውን ንጽጽር ይገልጻል።

5፥8 *ሰባቱን ከዋክብት፤* በአንድ ላይ የተሰበሰቡትን ሰባት ከዋክብት የሚያመለክት ነው፤ ይህ ብዙውን ጊዜ ኦሪዮን ከተባለው ኮከብ ጋር ተያይዞ የሚነገር ነው (የኢዮ9፥9ማብ ይመ)። *ጨለማን ወደ ንጋት ... ቀኑን አጨልሞ ሌሊት የሚያደርግ፤* የቀንንና የሌሊት መፈራረቅ ሥርዐት ነው (ከኤር31፥35 ጋር ያነጻጽሩ)። *የባሕሩም ውሃ፤* ከጠፈር በላይ ያሉትን ውሆች (9፥6፤ ዘፍ1፥7፤ እንዲሁም መዝ36፥8፤ 42፥7፤ 104፥3፡ 13 ማብ ይመ) ወይም ከባሕር በመትነን ወደ ላይ ወጥቶ በመጠራቀም እንደ ገና በዝናብ መልክ የሚወርደውን ውሃ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

*5፥10፤* በቍ7 የጀመረውን ግጥም አዘል አንቀጽ በዚህ ክፍል ይቀጥልና በቍ12ለ-13ላይ ያጠቃልላል፤ አንቀጹ ከቍ 11-12ሀ ላይ ሁለተኛ መደብ፣ ከቍ 12ለ-13 ደግሞ ሦስተኛ መደብ ተጠቅሞአል። በቍ7:10:12ለ-13 ላይ የሚገኘው ክስ ተጨባጭና በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን፣ በቍ11-12ሀ ላይ የተጠቀሰው ግን ቀጥተኛና ግልጽ ነው።

5፥11 *ብትሠሩም፤* እግዚአብሔር ያለአግባብ የሰበሰቡትንና የሚመሳሰሉትን ሀብታቸውን ይወስድባቸዋል። ብልጥግናቸውንም ወደ ሐዘን ይለውጣል (ከዘዳ28፥30፡38-40 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥13 *አስተዋይ ሰው፤* እንዲህ ያለ ሰው የመጣውን ሁኔታ መቀየር እንደማይችል ስለሚያውቅ ፍርድን ብቻ ይጠባበቃል።

5፥14 *በሕይወት ትኖሩ ዘንድ፤* ዐሳቡ በቍ4እና 6 ላይ ከሚገኘው ይልቅ በዚህ ስፍራ በግልጽ ተጠቅሶአል፤ ለውጡ በምን መንገድ መደረግ እንዳለበትም ተብራርቶአል። *መልካሙን፤* "እኔን" ፈልጉ (ቍ4) ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢሳ1፥16-17 እና የኢሳ1፥17 ማብ ይመ። *ከእናንተ ጋር፤* የሰላምና የበረከታችሁ ምንጭ በመሆን አብሮአችሁ ይሆናል ማለት ነው፡

5፥15 *ምናልባትም፤* የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደ ቀላል

ምናልባትም የሰራዊት ስምባክ እግዚአብሔር፣
ለዮሴፍ ትሩፍ ይራራ ይሆናል።

16ስለዚህ ጌታ የሰራዊት ስምባክ
እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
"በየመንገዱ ሁሉ ወየው ተብሎ
ይለቀሳል፤
በአደባባዩም የሥቃይ ጩኸት
ይሆናል፤ ገበሬዎች ለልቅሶ፣
አልቃሾችም ለዋይታ ይጠራሉ።
17በየወይኑ ዕርሻ ሁሉ ወየው ተብሎ
ይለቀሳል፤
እኔ በመካከላችሁ ዐልፋለሁና፤"
ይላል እግዚአብሔር ።

## የእግዚአብሔር ቀን

18የእግዚአብሔርን ቀን ለምትሹ፣
ለእናንተ ወዮላችሁ!
የእግዚአብሔርን ቀን ለምን ትሻላችሁ?
ያ ቀን ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን
አይደለም።
19ይህ ቀን አንድ ሰው ከአንበሳ ሲሸሽ፣
ድብ እንደሚያጋጥመው፣
ወደ ቤቱም ገብቶ፣ እጁን በግድግዳው
ላይ ሲያሳርፍ፣
እባብ እንደሚነድፈው ነው።
20የእግዚአብሔር ቀን ብርሃን ሳይሆን ጨለማ፣
የብርሃን ጸዳል የሌለው ድቅድቅ ጨለማ
አይደለምን?
21"ዓመት በዓላችሁን ተጸይፌአለሁ፤
ጠልቼውማለሁ፤
ጉባኤዎቻችሁ ደስ አያሰኙኝም።
22የሚቃጠል መሥዋዕትና የእህል
ቍርባን ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልቀበለውም፤
ከሰቡ እንስሶቻችሁ የኅብረት መሥዋዕት[ሀ]
ብታቀርቡልኝም፣
እኔ አልመለከተውም።
23የዝማሬህን ጩኸት ከእኔ አርቅ፤
የበገናህንም ዜማ አልሰማም።
24ነገር ግን ፍትሕ እንደ ወንዝ፣
ጽድቅም እንደማይደርቅ ምንጭ ይፍሰስ።
25 "የእስራኤል ቤት ሆይ፤ አርባ ዓመት
በምድረ በዳ፣
መሥዋዕትንና ቍርባንን አቅርባችሁልኝ ነበርን?
26ለራሳችሁ የሠራችሁትን፣
የንጉሣችሁን ቤተ ጣዖት፣
የጣዖቶቻችሁን ዐምድ፣
የአምላካችሁን[ሁ] ኮከብ አንሥታችሁ
ተሸከማችሁ።
27ስለዚህ ከደማስቆ ወዲያ እንድትሰደዱ አደ
ርጋችኋለሁ፤"
ይላል ስሙ የሰራዊት ስምባክ የሆነ
እግዚአብሔር።

## ተዘልላል ላለችው እስራኤል የተሰጠ ማስ ጠንቀቂያ

6 በጽዮን ተዘልላችሁ የምትቀመጡ፣
በሰማርያ ተራራ ያለ ሥጋት የምትኖሩ፣
የእስራኤልም ሕዝብ ለርዳታ ወደ እናንተ
የሚመጡባችሁ፣

5፥16 ኤር7፥34፤ 9፥17፤ኢል1፥11፤ አሞ8፥3፤ሰፎ1፥10
5፥17 ዘፀ11፥6፤ 12፥12፤ኢሳ16፥10፤ ኤር48፥33
5፥18 1ሳሙ2፥9፤ ኢዮ20፥28፤ ኢሳ2፥12፤5፥19፡ 30፤ኤር30፥5፡7፤ ኢል1፥15፤2፥2
5፥19 ዘዳ32፥24፤ ኢዮ20፥24፤ መክ10፥8፤ ኢሳ24፥17-18፤ ኤር15፥2-3፤48፥44፤ ሰቆ3፥10
5፥20 1ሳሙ2፥9፤ ኢሳ13፥10፤ ሕዝ7፥7፤አብ1፥15፤ ሰፎ1፥15
5፥21 ዘሌ26፥3፤ ኤር44፥4፤ ሕዝ23፥18፤ሆሴ2፥11
5፥22 ዘሌ26፥31፤ መዝ40፥6፤ ኢሳ1፥11-16፤ ኤር7፥21፤14፥12፤ አሞ4፥4፤ሚክ6፥6-7
5፥23 አሞ6፥5
5፥24 ኢሳ45፥8፤ ኤር22፥3፤ሚክ6፥8
5፥25 ዘፀ16፥35፤ ኢሳ43፥23
5፥26 ሕዝ18፥6፤ 20፥16
5፥27 ዘዳ32፥ 17-19፤ ኤር38፥17፤ አሞ4፥13፤6፥7፤7፥11 ፡17፤ሚክ1፥16፤ ሐዋ7፥42-43 አሞ3፥9፤ሰፎ1፥12፤ ሉቃ6፥24

6፥1 ኢዮ24፥23፤ኢሳ32፥9-11፤

[ሀ]22 *የሰላም መሥዋዕት* በመባል የሚታወቀው ነው።
[ሁ]26 *ወይም ንጉሣችሁን ሱኮትን ከፍ ከፍ አደረጋችሁት። እንዲሁም ጣዖታችሁን ቀይዋን የከዋክብት አማልክታችሁን፣ ሰብዓ ሊቃናት የሞሌክን ቤተ ጣዖት እንዲሁም የአምላካችሁን የሬፋንን ከዋክብት ከፍ አደረጋችሁ*

ነገር አድርጎ የመቈጠርን አደገኛነት ያመለክታል። ግልጽ የባሕርይ ለውጥ ያገኘውን ሰው እንኳ ቢሆን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ጊዜ መውሰድ ያስፈልጋል። *ትሩፍ፤* ሕዝቡ በአጠቃላይ ቢጠፋም እንኳ የአሁኑ ለውጥ የሚተርፉትን ጥቂቶችን ሊጠቅም እንደሚችል ያመለክታል ።

*5፥16-17፤* ይህ ክፍል ወደ ጀመረው የእንጉርጉሮ ዋና ሐሳብ ይመልሳል (ቍ1-2)። *በየመንገዱ...በአደባባዩም...ገበሬዎች... በየወይኑ ዕርሻ፤* ሁሉም የእግዚአብሔር ፍርድ ሰለባ ይሆናሉ፤ ለእንዲህ ዐይነቱ ነገር ጊዜ የሌላቸው ገበሬዎች እንኳ ሳይቀሩ ከአልቃሾች ጋር ሆነው ያለቅሳሉ፤ ለቅሶው ከከተማ እስከ ወይን ቦታዎች ይደርሳል። በግብፅ እንዳደረገው ሁሉ (ዘፀ12፥12) ቅዱሱ እግዚአብሔር ሲያልፍ ያልተቀደሱና የረከሱ ከቅጣቱ ሊያመልጡ ጨርሶ አይችሉም (ከኢሳ6፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

5፥18 *የእግዚአብሔርን ቀን፤* እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ጌታ መሆኑን በመግለጥ በዓለም ላይ ድል አድራጊነቱን የሚያሳይበት ቀን ነው (የ8፥9፤ ኢሳ2፥11፡17፡20 ማብ ይመ)። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ መሆናቸው ከፍ ከፍ የሚሉበትን የዚያን ቀን መምጣት በጕጕት ይጠባበቁ ነበር። ያ ቀን የብርሃን ቀን ይሆንልኛል (ቍ20) ብላ እስራኤል እንደ ጠበቀችው ሳይሆን የጨለማ ቀን እንደሚሆን አሞጽ ያስጠነቅቃል፤ እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበረችምና (በ1ቆሮ1፥8፤ 3፥12-15፤5፥5፤ 2ቆሮ1፥14፤ ፊል1፥6፡10፤2፥16 ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)። አሞጽ ስለ መጨረሻው ቀን ብቻ ሳይሆን በእስራኤል ላይ ስለ ተወሰነውና በቅርቡ በእስራኤል ላይ ስለሚሆነው ታላቅ ፍርድ ይናገራል።

*5፥19-20፤* በቍ19 ላይ የተገለጡት ሁለቱ ሥዕላዊ መግለጫዎች የሚመጣውንና ሊያመልጡት የማይቻለውን የእግዚአብሔር ፍርድ ያመለክታሉ።

*5፥21-27፤* በዚህ ክፍልም ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆንን በመግለጽ እስራኤልን በድጋሚ ይከስሳታል።

*5፥21-23፤* እነዚህ ሦስት ጥቅሶች በወቅቱ የነበረውን የእስራኤልን ሃይማኖታዊ ተግባራት ይቃወማሉ። ስሕተቱ በአምላኪዎችና በአምልኮ ሁኔታቸው ላይ እንጂ መንፈሳዊ ተቋማት በራሳቸው ምንም ስሕተት አልነበራቸውም። አካሄዳቸው ለእግዚአብሔር ሕግ አለመታዘዛቸውን ስለሚያንጸባርቅ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበት ምንም መሠረት አልነበራቸውም (ኢሳ1፥11-15 እና ማብ ይመ)።

5፥24 *ፍትሕ ... ጽድቅ፤* በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያስገኙ ተቀዳሚ ነገሮች ናቸው፤ ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ተቃውመውትና ንቀውት ነበር (ከቍ7፡10፡12 ጋር ያነጻጽሩ)። *ወንዝ... እንደማይደርቅ ምንጭ፤* ንጽጽር የተደረገው በዓመት ውስጥ በአብዛኛው ከሚደርቁ ምንጮች ጋር ነው። ንጽጽሩ ትክክለኛ ነው፤ ይኸውም ውሃ ባለበት የእንስሳትና የተክሎች ሕይወት እንደሚለመልም ሁሉ፣ ጽድቅና ፍትሕ ባለበት ቦታም የሰው ሕይወት ይለመልማል።

*5፥25፤* እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ለነበራቸው ኅብረት ዋና መሠረቱ መታዘዛቸው እንጂ የሚያቀርቡት መሥዋዕት አልነበረም (1ሳሙ15፥22-23ይመ፤ ከሮሜ1፥5ጋር ያነጻጽሩ)። *አርባ ዓመት በምድረ በዳ፤* ዘኍ14፥32-35ይመ

*5፥26፤* ጥቅሱ ግልጽ ባይሆንም፣ የእስራኤልን ጣዖት አምልኮ ያመለክታል፤ ነገር ግን ይህ አምልኮ የተደረገው ጥንት በምድረ በዳ ወይም በቅርቡ በተስፋፉት ምድር፣ አሊያም ሁለቱንም የተመለከተ ወይም በግልጽ አይታወቀም። የዚህ ጥቅስ አማራጭ ትርጕም ሁለት የተጸውዖ ስሞችን ከአካዳውያን ቋንቋ ወስዷል። የብሉይ ኪዳን የግሪኩ ትርጕም ወይም የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከተለየ ምንባብ ጋር ያዘምደዋል፤ በማያያዝም የሐሥ7፥42-43 ይጠቅሳል።

*5፥27፤* ይህ የመጨረሻው ቅጣት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ምድር ወጥተው ራቅ ወዳለ የባዕድ ምድር ተማርከው ይሄዳሉ ።

6፥1 *በጽዮን ... በሰማርያ ተራራ፤* በመሠረቱ አሞጽ የተናገረው ለእስራኤልን ቢሆንም፣ ይሁዳ ወይም ጽዮን የእግዚ

እናንት የአሕዛብ አለቆች ሆይ፤
ወዮላችሁ!
2 ወደ ካልኔ ሂዱ፤ እርሱንም ተመልከቱ፤
ከዚያም ወደ ታላቂቱ ሐማት ሂዱ፤
ወደ ፍልስጥኤም ከተማ ወደ ጌትም ውረዱ፤
እነዚህ ከሁለቱ መንግሥታቶቻችሁ
ይሻላሉን?
የምድራቸውስ ስፋት ከእናንተ ይበልጣልን?
3 ክፉውን ቀን ለምታርቁ፣
የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ ወዮላችሁ!
4 በዝሆን ጥርስ ባጌጠ ዐልጋ ላይ ለምትተኙ፤
በድንክ ዐልጋችሁ ላይ ለምትዝናኑ፣
ከበጎች መንጋ ጠቦትን፣
ከጋጣም ጥጃን ለምትበሉ፤
5 ባልተቃኘ በገና ለምትዘፍኑ፣
በሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት ለምትሹ፣
6 በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ፣
ምርጥ ሽቱም ለምትቀቡ፣
ስለ የሴፍ መከራ ግን ለማታዝኑ ወዮላችሁ!
7 ስለዚህ እናንተ በመጀመሪያ በምርኮ
ከሚወሰዱት መካከል ናችሁ፤
መፈንጠዛችሁና መዝናናታችሁም ያበቃል።

## እግዚአብሔር የእስራኤልን ትዕቢት ይጸየፋል

8 ጌታ እግዚአብሔር "የያዕቆብን ትዕቢት
ተጸይፌአለሁ፤
ምሽጎቹንም ጠልቻለሁ፤
ከተማይቱንና በውስጥዋ ያለውን ሁሉ፣
አሳልፌ እሰጣለሁ" ሲል በራሱ ምሎአል፤
ይላል የሰራዊት ስምባክ እግዚአብሔር።
9 በአንድ ቤት ውስጥ ዐሥር ሰዎች ቢቀሩ
እነርሱም ይሞታሉ። 10 በድኖቹንም ከቤት
አውጥቶ ማቃጠል ያለበት አንድ ዘመድ
መጥቶ ተደብቆ ያለውን ሰው፣ "ከአንተ ጋር
የቀረ ሌላ ሰው አለን?" ሲለው፣ እርሱም

6፥2 ዘፍ10፥10፤ ኢሱ11፥22፤2ነገ 17፥24፤2ዜና26፥6፤ ኤር49፥23፤ናሆ3፥8
6፥3 ኢሳ56፥12፤ ሕዝ12፥22፤አሞ9፥10
6፥4 አስ1፥6፤ ምሳ7፥17፤ ኢሳ1፥11፤ ሕዝ34፥2-3፤ አሞ3፥12
6፥5 1ዜና15፥16፤ መዝ137፥2፤ ኢሳ14፥11፤አሞ5፥23
6፥6 ኢሳ28፥1፤ ሕዝ9፥4፤16፥49፤ አሞ2፥8
6፥7 አሞ 5፥27
6፥8 ዘፍ22፥16፤ ዘሌ26፥19:30፤ ዘዳ32፥19፤መዝ47፥4 1ኤር12፥8፤አሞ4፥2፤ ዕብ6፥13
6፥9 አሞ5፥3
6፥10 1ሳሙ31፥12፤ አሞ8፥3
6፥11 ኢሳ34፥5፤ 55፥11፤አሞ3፥15
6፥12 ኢሳ1፥21፤ ሆሴ10፥4፤አሞ3፥10፤ 5፥7
6፥13 ኢዮ8፥15፤ ኢሳ28፥14-15
6፥14 ዘኍ13፥21፤ ኤር5፥15፤አሞ3፥11
7፥1 ቍ7፤ መዝ78፥46፤ኤር51፥ 14፤ኢል1፥4፤አሞ8፥1
7፥2 ዘፀ10፥15፤ ኢሳ37፥4፤ሕዝ 11፥13፤አሞ4፥9

"የለም" ይለዋል፤ ከዚያም በኋላ፣ "ዝም
በል፤ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት አይገ
ባንም" ይለዋል።
11 እነሆ፤ እግዚአብሔር ትእዛዝ ሰጥቶአልና፤
ታላላቅ ቤቶችን ያወድማቸዋል፤
ትንንሾቹንም ያደቅቃቸዋል።
12 ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይሮጣሉን?
ሰውስ እዚያ ላይ በበሬ ያርሳልን?
እናንተ ግን ፍትሕን ወደ መርዝነት፣
የጽድቅንም ፍሬ ወደ መራራነት
ለወጣችሁ።
13 እናንተ ሎዶባርን[a] በማሸነፋችሁ ደስ ያላችሁ፣
"ቃርናይምን[b] በራሳችን ብርታት ይዘናል"
የምትሉ፣
14 ሁሉን የሚገዛ ስምባክ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላልና፣
"የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፤ እነሆ፤ እኔ ከሐማት
መግቢያ[c] እስከ ዓረባ ሸለቆ ድረስ፣
የሚያስጨንቃችሁን ሕዝብ፣ በእናንተ
ላይ አስነሣለሁ።"

## አንበጣ፣ እሳትና ቱንቢ

7 ጌታ እግዚአብሔር ይህን አሳየኝ፤ የንጉሡ
የመከር እህል ከተሰበሰበ በኋላ ገበው
መብቀል በጀመረ ጊዜ፣ እርሱ የአንበጣ መንጋ
እንዲፈለፈል አደረገ። 2 አንበጦች የምድሩን
ሣር ግጠው ከጨረሱት በኋላ፣ "ጌታ እግዚ
አብሔር ሆይ፤ ይቅር እንድትል እለምንሃ
ለሁ፤ ያዕቆብ ይህን እንዴት ሊቋቋመው
ይችላል? ታናሽ ነው እኮ!" አልሁ።

[a]13 ትርጕሙ *ምንም* ማለት ነው።
[b]13 *ቃርናይም* ትርጕሙ *ቀንዶች* ማለት ነው፤ ቀንድ የጥንካሬ
*ምልክት* ነው።
[c]14 ወይም *ከመግቢያው ጀምሮ*

አብሔር ተግሣጽ ይገባት ነበር (ከ2፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ እስራኤል ሲባል ዐሥራ ሁለቱን ነገድ በሙሉ የሚመለከት ነበር። *የአሕዛብ አለቆች*፤ እስራኤል በራሷ እይታ አዲስ ኀይልና ብልጥግና በማግኘት እንደ ተመቻት በምትቈጥርበት ወቅት ማለት ነው።

*6፥2* ካልኔና ሐማት የወደቁት በዳግማዊ ኢዮርብዓም ዘመቻ (2ነገ14፥28)፣ የጋትም ቅጥር የፈረሰው በዖዝያን (2ዜና 26፥6) ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ ቃሎች የተነገሩት በእስራኤል ሕዝብ (ቍ1) ነው፣ ይኸውም፣ ሕዝቡ በመሪዎቻቸው ፊት በቀረብ ጊዜ ከንቱነታቸውን በመግለጽ ፊንታ እያሞጋገሱና እያቈላመጡ በትዕቢታቸው እንዲጸኑ ያደርጉ ነበር።

6፥4 *በዝሆን ጥርስ*፤ 3፥15 እና ማብ ይመ።

6፥5 *እንደ ዳዊትም*፤ 1ሳሙ16፥15-23፤2ሳሙ23፥1 ይመ።

6፥6 *ዮሴፍ*፤ የ5፥6 ማብ ይመ።

6፥8 *በራሱ ምሎአል*፤ የዘፍ22፥16 ማብ ይመ፤ ከዕብ 6፥13-14 ጋር ያነጻጽሩ። እግዚአብሔር በዚህ መሐላ የፍርዱ ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን ተናግሮአል።

*6፥10-11*፤ ይህ አስፈሪ ሁኔታ ነው። ከሞት የተረፈው ሰው በፍርሀት በቤቱ ውስጥ ተደብቆአል፤ ዘመዱም እንዳይጸልይ ወይም የእግዚአብሔርን ስም እንዳይጠራ ይከለክለዋል፤ የእግዚ አብሔር ቍጣ በከተማዪቱ ላይ ወድቆአልና።

6፥10 *በድኖቹንም... ማቃጠል*፤ ስለ ሞቱት ሰዎች ክብር መታሰቢያ እሳት ማቃጠልን የሚያመለክት ነው (ኤር34፥5 ይመ )። በክፉዎች ላይ ከሚፈጸመው በስተቀር በድን ማቃጠል በመሠረቱ የተለመደ አልነበረም (ዘሌ20፥14፤21፥9፤ኢሱ7፥15:25 ይመ፤ ከ1ሳሙ31፥11-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

6፥11 *ታላላቅ ቤቶችን...ትንንሾቹንም*፤ በ3፥15 ላይ ከተገለጸው የበጋ ቤትና የክረምት ቤት ጋር ያነጻጽሩ።

6፥12 *እዚያ ላይ በበሬ ያርሳልን*፤ የዕብራይስጡ ትርጕም አንዳንድ ትንሽ ለውጥ በማድረግ፣ "ባሕሩን በበሬ ያርሳልን?" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። እስራኤል ፍትሕን ስታጣምም በሰው ዘንድ ትክክለኛ ሥርዐት ለመሆኑ በግልጽ የሚታወቀውን ነገር ሁሉ በመቃወም ትፈጽማለች።

6፥13 *ሎዶባርን... ቃርናይምን*፤ የእነዚህን ቦታዎች ስምፍች በተመለከተ አሞጽ የተጠቀመበትን ምጸታዊ የቃላት ጨዋታ ከአግራጭ ትርጕሙ ይመ። እነዚህ ቦታዎች ዮአስ ከአዛሄል እጅ መልሶ የወሰዳቸው ሳይሆኑ አይቀሩም (2ነገ10፥32-33፤13፥25)፤ ከዚያም ወዲያውኑ ከአሞጽ ዘመን በኋላ የአሕዛብ ወገን በሆኑት በአሦራውያን ተወሰዱ (ቍ14፤ 2ነገ15፥29)። ከዚህም በመቀጠል በተከታታይ በተደረጉ ጥቃቶች በዳግማዊ ኢዮርብዓም ተይዞ የነበረው ግዛት ሁሉ ተወሰደ።

6፥14 *ከሐማት መግቢያ እስከ ዓረባ ሸለቆ*፤ በሰሜን ሊባኖስ ካለው ከኦሮንቴስ ወንዝ እስከ ሙት ባሕር ያለው ግዛት ይኸውም መላይቱን ምድር ማለት ነው (ከ2ነገ14፥25 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥1 *አሳየኝ*፤ የእግዚአብሔር መልእክት በማየትም ሆነ በመስማት በራእይ መልክ የሚቀርብበትን ሁኔታ ያመለክታል (ቍ4:7፤8፥1 ይመ፤ ከ9፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። *የንጉሡ የመከር እህል*፤ ከላዩ ላይ ለቤተ መንግሥት የሚሆን ግብር የሚነሣለት ቀደም ብሎ የሚደርሰው መከር ነው። *ገበው*፤ የመጀመሪያው እህል ከታጨደና ነዶው ተከምሮ መሬቱ ባዶ ከሆነ በኋላ የሚበቅለውን እህል ያመለክታል። የበጋ ድርቅ መጥቶ ሁሉን እስከሚያደርቅ ድረስ በዚህ መሬት ላይ የከብትና የበግ መንጋ ይሰማራበታል (ከ1ነገ18፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። *የአንበጣ*፤ ከ4፥9፤ከኢል1፥4 ጋር ያነጻጽሩ።

*7፥2*፤ ቍ5 ይመ። *ያዕቆብ*፤ እስራኤል ነው። *እንዴት ሊቋቋመው ይችላል*፤ ሕዝቡ ሁሉ በራብ መሠቃየቱን ያመለክታል። *ታናሽ*፤ የሚደርስበትን መከራ ለመቋቋም ዐቅም የለውም። አሞጽ እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳን በዚህ ስፍራ

[3]እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤
እግዚአብሔርም ይህ አይፈጸምም አለ።
[4]ጌታ እግዚአብሔር ይህንም አሳየኝ፤ ጌታ
እግዚአብሔር በእሳት ሊፈርድ ተዘጋጀ፤
እሳቱም ታላቁን ጥልቅ አደረቀ፤ ምድሪቱንም
በላ። [5]ከዚያም በኋላ፣ "ጌታ እግዚአብሔር
ሆይ፤ እንድትተወው እለምንሃለሁ፤ ያዕቆብ
ይህን እንዴት ሊቋቋመው ይችላል? ታናሽ
ነው እኮ! አልሁ።

[6]እግዚአብሔር ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤
ጌታ እግዚአብሔር፣ "ይህም ደግሞ አይ
ፈጸምም" አለ።

[7]ይህንም ደግሞ አሳየኝ፤ ጌታ በእጁ ቱምቢ
ይዞ በቱምቢ በተሠራ ቅጥር አጠገብ ቆሞ
ነበር። [8]እግዚአብሔርም፣ "አሞጽ፣ የምታየው
ምንድነው?" አለኝ።

እኔም፣ "ቱምቢ" አልሁ።

ጌታም እንዲህ አለ፤ "እነሆ፤ በሕዝቤ በእስራ
ኤል መካከል ቱምቢ እዘረጋለሁ፤
ከእንግዲህም ወዲያ አልምራቸውም።

[9]"የይስሐቅ ማምለኪያ ኮረብታዎች ባድማ
ይሆናሉ፤
የእስራኤል መቅደሶች ይፈርሳሉ፤
በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሰይፌ
እነሣለሁ።"

## አሞጽና አሜስያስ

[10]ከዚህ በኋላ የቤቴል ካህን አሜስያስ
ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮርብዓም እን

7፥3 ዘፀ32፥14፤ ዘዳ32፥36፤ኤር18፥8፤ 26፥19፤ሆሴ11፥8
7፥4 ዘዳ32፥22፤ ኢሳ66፥16፤ኢል1፥19
7፥5 ቍ1:2፤ ኢል2፥17
7፥6 ዘፀ32፥14፤ ኤር18፥8፤42፥10፤ ሕዝ9፥8፤ዮና3፥10
7፥8 2ነገ21፥13፤ ኤር1፥11:13፤15፥6፤ ሕዝ7፥2-9፤አሞ8፥2
7፥9 ዘሌ26፥30: 31፤1ነገ13፥34፤2ነገ 5፥9፤ኢሳ63፥18፤ ሆሴ10፥8
7፥10 ኢሱ7፥2፤ 2ነገ14፥23:24፤ ኤር26፥8-11፤38፥4
7፥11 ኤር36፥16፤ አሞ5፥27
7፥12 1ሳሙ9፥9፤ ማቴ8፥34
7፥13 ኢሱ7፥2፤ 1ነገ12፥29፤ኤር20፥2 ፤36፥5፤አሞ2፥12፤ ሐሥ4፥18
7፥14 1ሳሙ10፥5፤ 1ነገ10፥27፤2ነገ2፥5፤ 4፥37፤ኢሳ9፥10፤ ዘካ13፥5
7፥15 ዘፍ37፥2፤ 2ሳሙ7፥8፤ኢሳ6፥9፤ ኤር7፥1-2፤26፥12፤ ሕዝ2፥3-4
7፥16 ኤር22፥2፤ ሕዝ20፥46፤ሚክ2፥6
7፥17 2ነገ17፥6፤ ሕዝ4፥13፤ ሆሴ4፥13፤9፥31 አሞ2፥12-13፤5፥27

ዲህ ሲል መልእክት ላከ፤ "አሞጽ በእስራኤል
ቤት መካከል በአንተ ላይ እያሤረ ነው፤
ምድሪቱም ቃሉን ሁሉ ልትሸከም አትችልም፤
[11]አሞጽ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበርና፤

" 'ኢዮርብዓም በሰይፍ ይሞታል፤
እስራኤልም በእርግጥ ከትውልድ አገሩ
ተማርኮ ይሄዳል።"

[12]አሜስያስም፣ አሞጽን እንዲህ አለው፤
"አንተ ባለ ራእይ ከዚህ ሂድ! ከይሁዳ ምድር
ሽሽ፤ እዚያም እንጀራህን ብላ፤ በዚያም ትንቢት
ተናገር። [13]ከእንግዲህ ወዲያ ግን በቤቴል
ትንቢት አትናገር፤ የንጉሡ መቅደስ፣ የመ
ንግሥቱም መኖሪያ ነውና።"

[14]አሞጽም ለአሜስያስ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"እኔ እረኛና የባሉጥ ፍሬ ለቃሚ ነኝ እንጂ
ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤ [15]እግዚ
አብሔር ግን የበግ መንጋ ከምጠብቅበት ቦታ
ወስዶ፣ 'ሂድና ለሕዝቤ ለእስራኤል ትንቢት
ተናገር' አለኝ፤ [16]እንግዲህ የእግዚአብሔርን
ቃል ስማ።
አንተ፣ " 'በእስራኤል ላይ ትንቢት አትናገር፤
በይስሐቅም ቤት ላይ አትስበክ' ትላለህ።
[17]"ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤"

'ሚስትህ በከተማዪቱ ውስጥ ጋለሞታ
ትሆናለች፤
ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም በሰይፍ ይወድቃሉ፤
ምድርህም እየተለካ ይከፋፈላል፤
አንተ ራስህ በረከሰ[ሾ] ምድር ትሞታለህ፤

[ሾ]17 ዕብራይስጡ ርኩስ ይለዋል።

አልጠቀሰም፤ ምክንያቱም እስራኤል ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ እንጻር ታማኝ ሆና ባለመገኘቷ ይህን መብት መጠቀም ስላል ቻለ ይሆናል።

*7፥3፤* ቍ6 ይመ። *እግዚአብሔር …ተጸጸተ፤* ለነቢያት ምልጃ የተሰጠ ምላሽ ነው (ከዘፍ 20፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይቅርታ ግን አልተደረገም።

7፥4 *ታላቁን ጥልቅ፤* የሜድትራኒያንን ባሕር ሊሆን ይችላል። *ምድሪቱንም፤* ምናልባት የተሰፋዪቱን ምድር፣ በይበልጥም በምድ ሪቱ ላይ የበቀለውን ሁሉ ሊያመለክት ይችላል (ከኢል1፥19ጋር ያነጻ ጽሩ)

*7፥5፤* የቍ2 ማብ ይመ

*7፥6፤* የቍ3 ማብ ይመ

*7፥7፤* እስራኤል በቱንቢ ከተሠራ ቅጥር ጋር ተነጻጽራ ቀርባለች፤ እግዚአብሔር ካደረገላት ነገር የተነሣ መሆን ይገባት የነበረውን ነገር ያመለክታል።

*7፥8-9፤* ከቍ1-6 በተገለጸው ላይ እግዚአብሔር አጠቃላይ ጥፋትን የሚያስከትል ከባድ ቅጣት ለማድረግ መወሰኑ ተጠ ቅሶአል፣ ይቅርታ ለማድረግ ቃል ባይገባም፣ በአሞጽ ጩኸት ከጽኑ ቍጣው ተመልሶአል። ከዚህ በኋላ ግን እግዚአብሔር ለእንዲህ ዐይነቱ ቀጣይ ምልጃ በሩን ክፍት አላደረገም (ከኤር7፥16፤ 11፥14፤ 14፥11፤15፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

7፥8 *ቱምቢ፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ "የተሠራው" (ቍ7) በእግዚአብሔር መለኪያ መሠረት ነው፤ ስለ ሆነም ከመለኪያው ደረጃ በታች እንዲሆን አይገባውም ነበር፤ ነገር ግን በተለካ ጊዜ ከመለኪያው ደረጃ በታች ሆኖ ተገኘ(ከ2ነገ21፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። *በሕዝቤ፤* በአሞጽ መጽሐፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እስራኤልን፣ "ሕዝቤ" ብሎ ይጠራል(ቍ15፤ 8፥2፤ 9፥10:14 ይመ)። *ከእንግዲህም ወዲያ አልምራቸውም፤* 8፥2 ይመ።

7፥9 *ማምለኪያ ኮረብታዎች …መቅደሶች… ቤት፤* ሃይማኖታዊና ፓለቲካዊ ከበሬታን ማግኛ ማእከላት እንዲሁም መመጻደቂያ ትምክህቶች ይፈርሳሉ ማለት ነው። *የይስሐቅ፤* የእስራ ኤል ወይም የያዕቆብ አባት ስም ሲሆን፣ እስራኤልን በዚህ ዐይነት ሁኔታ የተጠቀሰው በአሞጽ መጽሐፍ ብቻ ነው (ቍ16 ይመ)።

*ኢዮርብዓም፤* ከምዕራፍ 1-6የተጠቀሰው ነገር በአጠቃላይ በእስራ ኤልና በሰማርያ ያሉትን መሪዎች የሚመለከት ሲሆን ፣በዚህ ስፍራ አሞጽ አንድን ሰው ብቻ ጠቅሷል፤ ይኸውም ንጉሡን ነው።

*7፥11፤* የአሜስያስ ቃል የአሞጽን መልእክት አስጥሮ ያቀርባል (የቍ17 ማብ ይመ)። *ኢዮርብዓም፤* የንጉሡ ስም ቤቱንና (ቍ9) ሥርወ መንግሥቱን ሊወክል ይችላል። *ይሞታል፤* ኢዮርብዓም ጊዜው ሲደርስ ሞተ (2ነገ14፥29)፤ ልጁና ወራሹ የሆነው ዘካርያስ ግን (2ነገ15፥8) በሰው ተገደለ (2ነገ15፥10)።

7፥12 *ባለ ራእይ፤* አሜስያስ፣ አሞጽን ቀም ነገረኛ እንዳ ልሆነ ቅጥረኛ ነቢይ በመቍጠር ትንቢት እንዳይናገር ከለከለው።

7፥13 *የንጉሡ መቅደስ* አሜስያስ ያገለገለው የሰማርያን ንጉሥ እንጂ "የእስራኤልን ሰማያዊ ንጉሥ" አይደለም፤ ስለዚህ በኢዮርብዓም ላይም ሆነ በቤተ መንግሥቱ ባለው መቅደስ ላይ ትንቢት እንዲናገር አልፈቀደም።

7፥14 *ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤* አሞጽ ቀደም ብሉ ከነቢያቱም ሆነ ከተከታዮቻቸው ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ገለጸ (የ1ነገ20፥35 ማብ ይመ)። በኢየሩሳሌምና በኢ ዮርብዓም ላይ የፍርድ ቃል እንዲናገር ማንም አልቀጠረውም። *እረኛ፤* የ1፥1 ማብ ይመ፤ ይሁን እንጂ የዕብራይስጡ ትርጒም ከዚህ ክፍል በስተቀር በሌላ ስፍራ የማይገኘውን ልዩ ቃል ይጠቀ ማል። ለዚህ ቃል የቀረበው የእብራይስጡ ቃል፣ "ከብት" ከሚለው ቃል ጋር ይቀራረባል፤ ስለዚህ አሞጽ ምናልባት በጎችን ብቻ ሳይሆን የከብት እረኛም እንደ ነበረ መገመት ይቻላል። *የባሉጥ ፍሬ፤* የበለስን ፍሬ የሚመስል ፍሬ የሚያፈራና በጣውላነት የሚያገለግል ትልቅ ዛፍ ነው። ጥሩ ፍሬ ለማግኘት፣ አትክልተኛው የእያንዳንዱን ፍሬ ጫፍ መግረዝ ነበረበት።

7፥15 *ከምጠብቅበት፤* 2ሳሙ7፥8 ይመ። *ሂድና፤* እግዚአብሔር በዚያ ትንቢት እንዲናገር ስለላከው፤ አሞጽ በቤቴል ነበር።

7፥16 *ትንቢት አትናገር፤* ከ2፥12 ጋር ያነጻጽሩ።

*7፥17፤* አሞጽ የእግዚአብሔርን ፍርድ በካህኑ ላይ ተናገረ፤ *ጋለሞታ፤* አሜስያስ ተሰዶ፣ ልጆቹም ሞተው የቤተ ሰቡ ርስት ከተወሰደ በኋላ የአሜስያስ ሚስት ኑሮን ለመግፋት ወደ ዝሙት አዳሪነት ተግባር ለመሰማራት ተገደደች። *ምድርህም፣* የአሜስያስ

እስራኤልም ከትውልድ አገሩ፣
ተማርኮ ይሄዳል::’ ”

### የጐመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት

8 ጌታ እግዚአብሔር ይህን አሳየኝ፤
እነሆ፤ የጎመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት
ነበረ:: 2እርሱም፣ “አሞጽ ሆይ፤ ምን ታያለህ?”
አለኝ:: እኔም፣ “የጎመራ ፍሬ የሞላበት ቅርጫት
አያለሁ” አልሁ:: ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር
እንዲህ አለኝ፤ “በሕዝቤ በእስራኤል ላይ
ፍጻሜ መጥቶአል፤ ከእንግዲህም አልምራ
ቸውም::”

3ጌታ እግዚአብሔር፣ “በዚያ ቀን የቤተ
መቅደሱ ዝማሬ ወደ ዋይታ[f] ይለወጣል፤
እጅግ ብዙ የሆነ የሰው ሬሳ ወድቆ ይገኛል፤
ዝምታም ይሰፍናል” ይላል::

4እናንት ችግረኞችን የምትረግጡ፣
የምድሪቱንም ድኾች የምታጠፉ ይህን ስሙ፤

5እንዲህም ትላላችሁ፤
“መስፈሪያውን በማሳነስ፣
ዋጋውን ከፍ በማድረግ፣
በሐሰተኛ ሚዛን በማጭበርበር፣
እህል እንድንሸጥ፣
የወር መባቻ መቼ ያበቃል?
ስንዴም ለገበያ እንድናቀርብ፣
ሰንበት መቼ ያልፋል?”
6ድኻውን በብር፣
ችግረኛውንም በጥንድ ጫማ እንገዛለን፤
ግርዱን እንኳ በስንዴ ዋጋ እንሸጣለን::”

7እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ሲል
ምሎአል፤ “እነርሱ ያደረጉትን ሁሉ ከቶ አል
ረሳም::

8“በዚህ ነገር ምድር አትናወጥምን?
በውስጧ የሚኖሩትስ ሁሉ አያለቅሱምን?

8፥1 አሞ7፥1
8፥2 ዘፍ40፥16፤ ኤር1፥13፤24፥3፤ ሰቆ4፥18፤ ሕዝ7፥2-9፤አሞ7፥8
8፥3 አሞ5፥16፤ 6፥10
8፥4 ኢዮ20፥19፤ መዝ14፥4፤ምሳ30፥14፤አሞ2፥7
8፥5 ዘፍ31፥7፤ ዘኍ10፥10፤ዘዳ25፥15፤2ነገ4፥23፤ነህ10፥31፤13፥15-16፤ ኢሳ58፥13 ሕዝ45፥10-12 ሆሴ12፥7፤ ሚክ6፥10-11፤ዘካ5፥6
8፥6 አሞ2፥6፤ 4፥1፤5፥11
8፥7 ኢዮ35፥15፤ መዝ47፥4፤ሆሴ8፥13
8፥8 ኢዮ9፥6፤ መዝ18፥7፤ኤር46፥8፤51፥29፤አሞ9፥5
8፥9 ኢዮ5፥14፤ ኢሳ59፥9-10፤ ኤር13፥16፤15፥9፤ ሕዝ32፥7፤ አሞ5፥8፤ሚክ3፥6፤ ማቴ27፥45፤ ማር15፥33፤ ሉቃ23፥44-45
8፥10 ዘፍ21፥16፤ ዘሌ13፥40፤ዘሌ26፥31፤ኢሳ3፥17፤ ኤር2፥19፤ሰቆ5፥15፤ ሕዝ7፥18፤ሆሴ2፥11፤ ኢል1፥8
8፥11 1ሳሙ3፥1፤ 2ዜና15፥3፤ኢሳ30፥20፤ ኤር30፥3፤31፥27
8፥12 ሕዝ20፥3:31
8፥13 ኢሳ9፥17፤ 41፥17፤ሆሴ2፥3
8፥14 1ነገ12፥29፤ መዝ46፥2፤አሞ5፥2:5፤ ሚክ1፥5

የምድር ሁለመና እንደ ዐባይ ወንዝ ይነሣል፤
እንደ ግብፅ ወንዝም ወደ ላይ ይፈናጠራል፤
ተመልሶም ይወርዳል::”
9ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በዚያ ቀን፣ ፀሓይ በቀትር እንድትጠልቅ
አደርጋለሁ፤
ምድርንም ደማቅ ብርሃን ሳለ በቀን
አጨልማታለሁ::
10ዓመት በዓላችሁን ወደ ልቅሶ፣
ዝማሬአችሁንም ሁሉ ወደ ዋይታ
እለውጣለሁ፤
ሁላችሁም ማቅ እንድትለብሱ፣
ጠጕራችሁንም እንድትላጩ አደርጋለሁ፤
ያን ጊዜ ለአንድያ ልጅ ሞት እንደሚለቀስበት፣
ፍጻሜውንም እንደ መራራ ቀን
አደርገዋለሁ::”

11ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“በምድር ላይ ረሐብን የምሰድበት ዘመን
ይመጣል፤
ይኸውም የእግዚአብሔርን ቃል
የመስማት ረሐብ እንጂ፣
እንጀራን የመራብ ወይም ውሃን
የመጠማት አይደለም::
12ሰዎች እግዚአብሔርን ለመሻት፣
ከባሕር ወደ ባሕር፣
ከሰሜን ወደ ምሥራቅ ይንከራተታሉ፤
ነገር ግን አያገኙትም::
13“በዚያ ቀን፣
“ቈንጆች ሴቶችና ብርቱዎች ጕልማሶች፣
ከውሃ ጥም የተነሣ ይዝላሉ::
14በሰማርያ ኀፍረት[f] የሚምሉ፣
ወይም፣ ‘ዳን ሆይ፤ ሕያው አምላክህን’
የሚሉ፣

[f]3 *የቤተመቅደሱ ዘማሪያን ዋይታ ያሰማሉ የሚሉ አሉ::*
[f]14 *ወይም በአሺማ ወይም በጣኦት አማልክት::*

የገል ይዞታ የነበረው ርስት ተወስዶ ለሌሎች ተከፋፍሉ ይሰጣል ማለት ነው:: *በረከስ ምድር፤* ጣዖት የሚመለክበት ምድር የረከሰ በመሆኑ፣ በሥርዐቱ መሠረት ለክህነት አገልግሎት የነበረው ቅድስና ይረክሳል ማለት ነው (አማራጭ ትርጕሙን ይመ):: *እስ ራኤልም ከትውልድ አገሩ፤* አሞጽ ይህን ሐረግ (በዕብራይስጡ) ደጋግሞ ይጠቅሳል፤ ይኸውም፣ አሜስያስ ቀደም ብሎ በአጭሩ ከገለጸው የአሞጽ መልእክት የመጨረሻው ሁለት መሥመር ነው::

8፥1 *አሳየኝ፤* የ7፥1 ማብ ይመ::

8፥2 *የጐመራ ፍሬ ... ፍጻሜ መጥቶአል፤* በዕብራይስጥ ቋንቋ ሁለት ትርጕም ያለው ኅብር አገላለጽ ነው፤ እስራኤል የም ትነቀልበት ጊዜ እንደ ደረሰ ያመለክታል::

8፥3 *በዚያ ቀን፤* የ5፥18 ማብ ይመ:: *ዋይታ... ዝምታም፤* በዚህ የመከር ጊዜ የሚኖረው የምስጋና መዝሙር ሳይሆን፣ ከጭ ንቀት የተነሣ የሚሆን ጸጥታ ነው (ከዘሌ23፥39-41 ጋር ያነጻጽሩ)::

8፥5 *የወር መባቻ ... ሰንበት፤* የንግድ ሥራ የማይካሄድ ባቸው የሃይማኖት በዓላት ናቸው (ከዘኍ28፥9-15 ጋር ያነጻጽሩ):: *መስፈሪያውን በማሳነስ፣ ዋጋውን ከፍ በማድረግ፤* በሐሰተኛ ሚዛን ማለት ነው::

*8፥6፤* የ2፥6 ማብ ይመ ::

8፥7 *በያዕቆብ ክብር ...ምሎአል፤* እግዚአብሔር አምላኳ ስለ ሆነ እስራኤል በዚህ ትመካለች::

8፥8 *እንደ ዐባይ ወንዝ ይነሣል፤* በኢትዮጵያ ወቅቱን ጠብቆ ከሚዘንበው ከባድ ዝናም የተነሣ የዐባይ ወንዝ ግብፅ ሲደርስ በየዓመቱ እስከ ሃያ አምስት ጫማ ከፍ ይላል፤ ከፍ ብለው ከተ ሠሩት መንደሮችና ከተሞች በስተቀር ጉርፉ መሬውን ሸለቆ ያጥለቀልቃል፤ ውሃውም ለም የሆነ ብዙ ዐፈር ይዞ ይሄዳል::

8፥9 *በዚያ ቀን፤* የ5፥18 ማብ ይመ:: *ምድርንም... አጨልማታ ለሁ፤* በሌላ ስፍራ እንደተጠቀሰው፣ “የእግዚአብሔር ቀን” ፍጥረት እንዳልነበር እስኪ መስል ድረስ የተፈጥሮ ሥርዐት በመዛባቱና ብርሃን ወደ ጨለማ በመለወጡ ይታወቃል (ኢሳ13፥10፤ 24፥23፤34፥4፤50፥3፤ ሕዝ32፥7-8፤ ኢል2፥10:31፤ ሚክ3፥6 ይመ)

8፥10 *ልቅሶ* ንጉሥ ዳዊት እንዳደረገው ነው (2ሳሙ18፥33):: *ማቅ እንድትለብሱ፣ ጠጕራችሁንም እንድትላጩ፤* የሐዘን ምልክት ነው (ዘፍ37፥34፤ ኤር4፥5ይመ)፤ አንድያ ልጅ ለወደ ፊት የቤተ ሰቡ የኑሮ መሠረት ስለ ሆነ ተስፋ ተደርጎ የሚጠበቅ ልጅ ነው (ከ2ሳሙ18፥18 ጋር ያነጻጽሩ):: *መራራ ቀን፤* የክብረ በዓል ቀን ተቃራኒ ነው (አስ 9፥22)::

8፥11 *ዘመን፤* የእግዚአብሔር ፍርድ ተግባራዊ መሆን በሚጀምርበት ጊዜ ማለት ነው:: *የእግዚአብሔርን ቃል የመስ ማት ራብ፤* በታላቅ ጭንቅ ጊዜ እስራኤል ተስፋን የሚያመለክት የትንቢትን ቃል ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ዘወር ብላለች (ለም ሳሌ 2ነገ 19፥1-4:14፤22፥13-14፤ ኤር21፥2፤ ሕዝ14፥3:7 ይመ)፤ ይሁን እንጂ በሚመጣው የፍርድ ጊዜ እግዚአብሔር ለእንዲህ ዐይነቱ ጥያቄ መልስ የሚሰጠው በዝምታ ነው፤ ይህም አስፈሪ የእግዚ አብሔር ዝምታ ነው (1ሳሙ28፥6፤ ሕዝ7፥26፤20፥1-3፤ ሚክ3፥4:7 ይመ)::

8፥12 *ከባሕር ወደ ባሕር፣ ከሰሜን ወደ ምሥራቅ፤* በመላው የእስራኤል ምድርና በዮርዳኖስ ማዶ ያለውን ምድር ሳይቀር ለማለት ነው::

8፥13 *ጥም፤* ሥጋዊ ጥማት ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ጥማትንም ሊያመለክት ይችላል:: ጕልበታቸው ተበልቶ አለቀ፤ ተወዳጆቹ ልጃገረዶችና ብርቱዎቹ ወንዶች ልጆች እንኳ ሳይቀሩ ዝለው ከጥቅም ውጭ ሆነዋል::

8፥14 *የሚምሉ፤* የሚምሉት በተለያዩ የማምለኪያ ስፍራ

ወይም ‘ሕያው የቤርሳቤህ አምላክን[x]’
ብለው የሚምሉ፣
ዳግመኛ ሳይነሡ፣ ለዘላለም ይወድቃሉ።”

## እስራኤል ትጠፋለች

9 ጌታን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ አየሁት፤
እርሱም እንዲህ አለ፤
“መድረኮቹ እንዲናወጡ፣
ጕልላቶቹን ምታ፣
በሕዝቡም ሁሉ ራስ ላይ ሰባብራቸው፤
የቀሩትን በሰይፍ እገድላቸዋለሁ፤
ከእነርሱ አንድም ሰው አይሸሽም፤
ቢሸሽም የሚያመልጥ የለም።
²መቃብር[1] በጥልቀት ቈፍረው ቢወርዱም፣
እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች፤
ወደ ሰማይ ቢወጡም፣
ከዚያ አወርዳቸዋለሁ።
³በቀርሜሎስ ጫፍ ላይ ቢሸሸጉም፣
አድኜ ፈልጌ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ፤
እይዛቸዋለሁም፤
በጥልቅ ባሕር ውስጥ ከእኔ ቢሸሸጉም፣
በዚያ እባቡ እንዲነድፋቸው አዘዋለሁ፤
⁴በጠላቶቻቸው ተነድተው ለምርኮ ቢወሰዱም፣
በዚያ እንዲገድላቸው ሰይፍን
አዛለሁ፤
ለመልካም ሳይሆን ለክፉ፣
ዐይኔን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ።
⁵ጌታ፣ እግዚአብሔር ጸባኦት፣
ምድርን ይዳስሳል፤
እርሷም ትቀልጣለች፤
በውስጥዋ የሚኖሩ ሁሉ ያለቅሳሉ፤
የምድር ሁለመና እንደ ዐባይ ወንዝ
ይነሣል፤
እንደ ግብፅ ወንዝም ይወርዳል።
⁶መኖሪያውን[m] በሰማይ የሚሠራ፣
መሠረቱንም[n] በምድር የሚያደርግ፣
የባሕርን ውሃ የሚጠራ፣
በምድርም ገጽ ላይ የሚያፈስ፣
እርሱ ስሙ እግዚአብሔር ነው።
⁷“እናንተ እስራኤላውያን፣
ለእኔ እንደ ኢትዮጵያውያን
አይደላችሁምን?”
ይላል እግዚአብሔር
“እስራኤልን ከግብፅ፣
ፍልስጥኤማውያንን ከከፍቶር[a]፣
ሶርያውያንንም ከቂር አላወጣሁምን?
⁸“እነሆ፤ የጌታ እግዚአብሔር ዐይኖች፣
በኀጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው፤
ከምድር ገጽ፣ ፈጽሜ አጠፋዋለሁ፤
የያዕቆብን ቤት ግን፣
ሙሉ በሙሉ አልደመስስም፤”
ይላል እግዚአብሔር።
⁹“እነሆ፤ ትእዛዝ እሰጣለሁ፤
እህል በወንፊት እንደሚነፋ፣
የእስራኤልን ቤት፣
በሕዝብ ሁሉ መካከል እንዲሁ አደርጋለሁ፤
ነገር ግን አንዲት ቅንጣት በምድር ላይ
አትወድቅም።
¹⁰በሕዝቤ መካከል ያሉ፣
‘ክፉ ነገር አያገኘንም ወይም አይደርስብንም’
የሚሉ፣
ኀጢአተኞች ሁሉ፣
በሰይፍ ይሞታሉ።

[x]14 ወይም ኀይል [1]2 ዕብራይስጡ ሲዖል ይለዋል። [m]6 ዕብራይስጡ ለዚህ ሐረግ የሰጠው ትርጕም ምን እንደሆነ አይታወቅም። [n]6 ዕብራይስጡ ለዚህ ሐረግ የሰጠው ትርጕም ምን እንደሆነ አይታወቅም። [a]7 በላይኛው ዐባይ አካባቢ ያለ ሕዝብ ነው

9፥1 መዝ68፥21፤ ኤር11፥11
9፥2 ኢዮ7፥9፤ ኤር51፥53፤ ሕዝ26፥20፤አብ1፥4
9፥3 ዘፍ49፥17፤ ኢዮ11፥20፤ መዝ68፥22፤139፥8-10፤ኢሳ27፥1፤ ኤር16፥16-17፤ አሞ1፥2
9፥4 ዘሌ26፥33፤ ኤር21፥10፤39፥16፤ 44፥11፤ሕዝ5፥12፤ 15፥7፥21 አሞ8፥8
9፥6 መዝ104፥1-3፥ 5-6፥13፤ኤር43፥9፤ አሞ5፥8
9፥7 ዘፍ10፥14፤ ዘዳ2፥23፤2ነገ16፥9፤2 ዜና12፥3፤ኢሳ20፥4፤ 22፥6፤43፥3፤ አሞ2፥10
9፥8 ኤር4፥27፤ 44፥27
9፥9 ኢሳ30፥28፤ ኤር31፥36፤ዳን9፥7፤ ሉቃ22፥31
9፥10 ኤር5፥12፤ 23፥17፤49፥37፤ ሕዝ20፥38፤አሞ6፥3
9፥11 ዘፍ26፥22፤ መዝ53፥6፤80፥12፤ ኢሳ7፥2፤49፥8፤ ሕዝ17፥24፤ ሚክ7፥8፥11፤ዘካ12፥7 ፤14፥10

ዎች ባሉት ሐሰተኛ አማልክት ነው (አማራጭ ትርጕሙን ይመ)፤ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ይልቅ በእነዚህ አማልክት ይታመኑ ነበር።

9፥1 *ጌታን…አየሁት፤* የ7፥1 ማብ ይመ። በዚህ ጊዜ እግዚ አብሔር በምድር ላይ ቆሞ ነበር። *በመሠዊያው አጠገብ፤* ሕዝቡ የሰላምና የበረከት ቃል ለመስማት በሚጠብቁበት ስፍራ፣ እግዚ አብሔር ጥፋትን ሊያመጣባቸው ተዘጋጅቶአል። *ጕልላቶቹን፤* በጌጣጌጥ ከተዋቡት ጕልላቶች ጀምሮ በታላላቅ ድንጋይ እስከ ታነጹት መድረኮች ድረስ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ሙሉ በሙሉ ያፈርሳል። የሚቀጥሉት ክፍሎች የሚደርሰውን ጥፋት ይገልጻሉ። በራእዩ ውስጥ እግዚአብሔር የሚታየው በኢየሩሳሌም ይሁን ወይም አይሁን ግልጽ አይደለም፤ ነገር ግን በቤቴል የቤተ መቅደስ ውቅር አለመኖሩን እናውቃለን።

*9፥2-4፤* እነዚህ ጥቅሶች ሊፈጸም ካለው የእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ እንደማይቻል ያመለክታሉ። አንድ ሰው ሊደር ስበት የሚችለው ሐሳባዊ፣ “ጥልቀት” የሚያመለክት ሲሆን፣ በመዝ 139፥7-12 ላይ ከተጠቀሰው ጋር ሊነጻጸር ይችላል። የእግዚአብሔር ግዛት ሲኦልን ሳይቀር የሚያካትት ነው (ቍ 2)።

9፥3 *በቀርሜሎስ ጫፍ፤* የ1፥2 ማብ ይመ። *እባቡ፤* በጣዖት አምላኪዎች ተረታ ተረት መሠረት እስፈሪውን የባሕር አውሬ የሚያመለክት ነው። ሁሉም ነገር በእርሱ ቍጥጥር ሥር ስለ ሆነ ማንም ሰው ወደ ጥልቁ ሄዶ በመሸሽ ከእግዚአብሔር ሊያ መልጥ አይችልም።

9፥4 *በጠላቶቻቸው ተነድተው… አዛለሁ፤* በሕዝቦች መካከል ተበታትነው ያሉት እንኳ ከእግዚአብሔር ፍርድ አያመልጡም። *ለክፉ ዐይኔን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ፤* ከመዝ33፥18፤ 34፥15 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥5 *ጌታ፤* ፈጣሪ የሆነው የእስራኤል አምላክ፣ ፍጥረተ ዓለ ማትን ሁሉ ደግፎ የሚይዝና የሚጠብቅ መሆኑን የሚናገር ዝማ ሬአዊ አገላለጽ ሲሆን፤ ይህም የተጠቀሱትን የፍርድ ቃሎች በበለጠ የሚያጠናክር ነው (ከ4፥13፤5፥8-9 ጋር ያነጻጽሩ)። *ምድርን… ትቀልጣለች፤* የመዝ46፥6 ማብ ይመ። *እንደ ዐባይ ወንዝ፤* 8፥8 እና ማብ ይመ።

9፥6 *መኖሪያውን በሰማይ፤* ምድር ስትናወጥ የሚፈርሰውን የሰውን መለኪያ፣ ከእግዚአብሔር መለኪያ ጋር ያነጻጽራል (ቍ 5)። መዝ104፥3 እና ማብውን ይመ። *የባሕርን፤* 5፥8 ማብ ይመ።

9፥7 *ኢትዮጵያውያን፤* ከግብፅ በስተ ደቡብ የሚኖሩ (እና ከአማራጭ ትርጕሙ ጋር ያነጻጽሩ) ጠቈር ያለ ቆዳ ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። *እስራኤልን… አላወጣሁምን?* የዘፀ20፥2 ማብ ይመ። እስ ራኤል ባለፉት ዘመናት እግዚአብሔር የሰጣት በረከት ወደፊት ለሚያደርግላት ቸርነት ዋስትና ሆኖአት በእርሱ ላይ መደገፍ አልቻለችም። በዕብሪት ላይ ከተመሠረተው ዐመፀኝነቷ የተነሣ እስራኤል በእርሱ ላይ ተስፋ ማድረግ አልቻለችም። የልቧ ትዕቢ ትና ዐመፀኝነት “በመውጣት” ዘመን ያገኘችው ልዩ ትርጕም እንዲወሰድባት አድርጉአል፤ ከግብፅ ወደ ከነዓን ያደረ ገችውም ጕዞ ሌሎች ሕዝቦች ካደረጉት ጕዞ የተለየ አልሆነም። *ፍልስጥኤ ማውያንን ከከፍቶር፤* የኤር 47፥4 ማብ ይመ። *ከቂር፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

9፥8 *በኀጢአተኛ መንግሥት፤* የተመረጠው ሕዝብ አለመ ታዘዝ ከሌሎች ሕዝቦች አለመታዘዝ ብሶ የተገኘውን እስራኤልን ማለት ነው (ከ1፥3-2፥16፤3፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)።

9፥9 *በወንፊት፤* ስንዴው ከመሬት ታፍሶ በሚነፋበት ጊዜ አብሮት የሚሰበሰበውን ጥቃቅን ድንጋይና ሌላ የማያስፈልግ ነገር ሁሉ ያጠራል። *አንዲት ቅንጣት …አትወድቅም፤* በወንፊት ሲነፋ እህሉ ብቻ ይቀራል፤ ሌላው ተጣርቶ ይጣላል።

9፥10 *ኀጢአተኞች ሁሉ… ይሞታሉ፤* ይህም የሚሆነው በዐመፀኝነታቸው ስለ ጸኑ ነው።

*9፥11፤* በአይሁድ ታልሙድ ይህ ጥቅስ ስለ መሲሑ እንደ ሚናገር ይታመናል። *እነሣዋለሁ፤* በአሞጽ የተነገረውን የፍርድ ቃል

## የእስራኤል መመለስ

[11] “በዚያ ቀን፣
የወደቀውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ፤
የተሰበረውን እጠግናለሁ፤
የፈረሰውን ዐድሳለሁ፤
ቀድሞ እንደነበረም አድርጌ እሠራዋለሁ፤
[12]ስለዚህ የኤዶምን ትሩፍ፣
በስሜ[ሀ] የተጠሩትንም ሕዝቦች ሁሉ
ይወርሳሉ፤”
ይላል ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር።
[13]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤
“እነሆ፤ ዐጫጁ ዐጭዶ ሳይጨርስ፣
ዐራሹ በላዩ የሚደርስበት፣
ቸግኝ ተካዩም ገና ተክሉ ሳይጨርስ፣
ወይን ጨማቂው የሚደርስበት ጊዜ
ይመጣል፤
አዲስ የወይን ጠጅ ከተራሮች
ይንጠባጠባል፤
ከኰረብቶችም ሁሉ ይፈሳል።
[14]የተሰደደውን[ለ] ሕዝቤን እስራኤልን
እመልሳለሁ፤
እነርሱም የፈራረሱትን ከተሞች መልሰው
ሠርተው በውስጣቸው ይኖራሉ።
የወይን ተክል ተክለው፣ ጠጁን ይጠጣሉ፤
አትክልት ተክለው ፍሬውን ይበላሉ።
[15]እስራኤልን በገዛ ምድራቸው እተክላቸዋለሁ፤
ከሰጠኋቸውም ምድር፣ ዳግመኛ
አይነቀሉም”
ይላል አምላክህ እግዚአብሔር።

9፥12 ዘኍ24፥18፤ ኢሳ43፥7፤ ኤር25፥29፤ ሐዋ15፥16-17
9፥13 ዘሌ26፥5፤ መሳ9፥27፤ ሩት2፥3፤ ኤር31፥38፤33፥14፤ ኢል2፥24፤3፥18
9፥14 2ነገ19፥29፤ ኢሳ32፥18፤ 49፥8፤61፥14፤62፥9፤ ኤር29፥14፤30፥18፤31፥28፤33፥7፤ ሕዝ28፥25-26፤ 34፥13-14፤አሞ5፥11
9፥15 ዘፀ15፥17፤ ኢሳ60፥21፤65፥9፤ ኤር3፥18፤18፥9፤23፥8፤24፥6፤32፥15፤ ሕዝ28፥26፤ 34፥25-28፤37፥12:35፤ኢል3፥20

ሀ12 ዕብራይስጡ እንደ ሰብዓ ሊቃናቱ ትርጉም የሕዝቡ ትሩፋትንና ስሜን የሚጠሩ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ።
ለ14 ወይም ዕጣ ፈንታቸውን አድሳለሁ እንደማለት ነው።

መሠረት በማድረግ ተስፋን የሚያድስ ነው፤ ይህም ከዘፍ3፥15 ጀምሮ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሚገኝ ቃል ነው፤ ይኸውም ከፍርድ በኋላ እግዚአብሔር በረከትን እንደሚያመጣና እስራኤልንም ፈጽሞ እንደማይተው ያመለክታል። *ድንኳን፤* በቀሙ፣ “ጎጆ”ማለት ሲሆን የዳዊትን ሥርወ መንግሥት ወይም የዐሥራ ሁለቱ ነገዶች ጥምር መንግሥት የሆነውን የዳዊትን መንግሥት ሊያመለክት ይችላል። “ጐጆ” የሚለው ቃል የተመረጠው የዳዊትን ከዝቅተኛ ቦታ መነሣት ለማስታወስ ይሆናል። *እንደነበረም፤* በዳዊትና በሰሎሞን ጊዜ እንደ ነበረው ለማለት ነው።

9፥12 *የኤዶምን ትሩፍ፤* እስራኤል ክተቀጣች በኋላ ከጨካኝ ጠላቶቿ የተረፈውን ሁሉ ለማለት ነው (የ1፥11 ማብ ይመ)። *በስሜ የተጠሩትንም ሕዝቦች ሁሉ፤* ዳዊት በእስራኤል ዙሪያ የነበሩትን ሁሉ እንደ ገዛ በማስታወስ፣ እግዚአብሔር የቀባው የወደ ፊቱ ንጉሥ የሚያስተዳድረው ግዛት ዳር ድንበር ከየት እስከ የት እንደሚዘልቅ የሚያመለክት ነው። ይህም ለአብርሃምና ለዳዊት የተደረጉ ኪዳኖች መፈጸማቸውን ያመለክታል። መሲሑ በኤዶም የተመሰሉትን የቀድሞ ጠላቶችን እንኳ ጨምሮ ይገዛል (የኢሳ34፥5 ማብ ይመ)። *ይህን የሚያደርግ፤* የተናገረውን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው።

*9፥13-15፤* ጥፋት፣ እጦትና ሞት እንደሚሆን ከተነበየ በኋላ (ከ5፥9፡11፡27 ጋር ያነጻጽሩ) የመጨረሻ ቃሉ ወቅቱ በመፈራረቅ መዝራትና ማጨድ የማይቋረጥበትንና አዲስ ምርት የሚታይበትን የከበረውን የገነትን ሕይወት በሥዕላዊ መልክ አቀረበ። ይህም በ4፥6-11 ከላይ ከተገለጸው ጋር የሚቃረን ነው።

*9፥13፤* ከኢል 3፥18 ጋር እንደሚመሳሰል ያስተውሉ።

9፥14-15፤*እመልሳለሁ ... ሠርተው ... ተክለው፤* በተስፋዪቱ ምድር እግዚአብሔር ሕዝቡን አምራች፣ ፍሬያማና ሰላማቸው የተጠበቀ ያደርጋቸዋል።

9፥14፤ *ሕዝቤን፤* የ7፥8 ማብ ይመ፤ ከሆሴ 1፥9 እንዲሁም ከሆሴ2፥23 ጋር ያነጻጽሩ። የፈራረሱትንም ከተሞች መልሰው ይሠራሉ፤ ኢሳ58፥12 እና ማብ ይመ።

9፥15 *ዳግመኛ፤* እስራኤል ለመጨረሻ ጊዜ ተመልሳ ሙሉ በሙሉ ከተገነባች በኋላ ዳግም አትደመሰስም። *አምላክህ፤* ከሆሴ1፥9 እንዲሁም ከሆሴ 2፥23 ጋር ያነጻጽሩ።